# የባሕሩ ላይ ምስክርነት

ለጸሎት ራሳችንን ከማኅንበሳችን በፊት፡ ከእግዚአብሔር ቃል የተወሰነ ክፍል ማንበብ እፈልጋለሁ። ሁልጊዜ ቃሉን ማንበብ እወዳለሁ፡ ምክንያቱም ቃሎቼ ይወድቃሉ፡ የሰው ናቸውና፡ ቃሉ ግን ሊወድቅ አይችልም። ዛሬ ማታ የሚነበበበውን ለምትከታተሉ፡ እና ሌሎቻችሁም፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 14ን፡ ከቁጥር 22 ጀምሮ፡ እናንብብ።

**ወዲያውም ሕዝቡን** ሲያሰናብት **ሳለ ደቀ መዛሙርቱ፡ በታንኳይቱ ገብተው፡ ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው።**

**ሕዝቡንም አሰናብቶ፡ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፡ በ... በመሸም ጊዜ፡ ብቻውን በዚያ ነበረ።**

**ታንኳይቱም አሁን በባሕር መካከል ሳለች፡ ነፋስ ከወደ ፊት ነበርና፡ በማዕበል ትጨነቅ ነበር።**

**ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ፡ ወደ እነርሱ መጣ።**

**ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፡ ምትሐት ነው፡ ብለው፡ ታወኩ፣ በፍርሃትም ጮኹ።**

**ወዲያውም ኢየሱስ፡ ተናገራቸውና፡ አይዞአችሁ፣ እኔ ነኝ፣ አትፍሩ አላቸው።**

2 አሁን ለጸሎት ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። ራሶቻችንና ልባችን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ብሎ ሳለ፡ ዛሬ ማታ፡ እጆቻችሁን ከፍ በማድረግ፡ በጸሎት ለመታወስ፡ ለእግዚአብሔር ማሳወቅ የምትፈልጉ፡ ፍላጎት አላችሁን? ጌታ ወደ እናንተ ይመልከት፡ ለእኛም ምህረት ያድርግልን።

3 ሰማያዊው አባታችን ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ስምና በኩል፡ አሁን ወደ መገኘትህ እንቀርባለን። ቃል በገባልን፡ በተባረከው፡ ማረጋገጫው፡ በሰሙ "ማንኛውንም ነገር ብንጠይቅ" እንደምትሰጠን፡ እናውቃለን። ስለዚህም እጅግ እናመሰግንሃለን። አሁን እየሰማኸን እንደሆነ፡ ያለንን እርግጠኛነት፡ በቃላት መግለጽ አንችልም።

4 ጌታ ሆይ፡ እነዚያን እጆች አይተሃል። ምን እንደሚያስፈልጋቸው አንተ ታውቃለህ። አንተ ሁሉን አዋቂ፡ ሁሉን ቻይ፡ ወሰን የሌለው አምላክ ነህ፡ የሰዎችንም ልብ እንደምታውቅ እናውቃለን። ሃሳባችንን ታውቀዋለህ። ከመፈጠራችን በፊትም፡ ሃሳባችንን ሁሉ ታውቀዋለህ፡ ምክንያቱም ፍጻሜ የሌለ አምላክ ነህና።

5 ጌታ ሆይ፡ በዚህ ሰዓት፡ ምኞታችን ወደ አንተ በሚደርሰበት ጊዜ፡ ከሰማይ ወደ ታች እንድትመለከት፡ እንጸልያለን፡ ጌታ ሆይ፡ ልመናችንን ወደ ልብህ ውሰደው፡ ጌታ ሆይ፡ በክብርህም ባለጠግነት መሠረት መልስ ስጠን። የአንተ መለኰታዊ ፈቃድ መሆኑን በመተማመን፡ የልባችንን ምኞት ስጠን። ደግሞም ፈቃድህን ማድረግ እንደሚያስደስትህ እናውቃለን።

6 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ደግመህ ታላቅ የመገኘትህን ክብር ሰጠን። የታመሙትን ፈውስ። የጠፉትን አድን፡ በኃጢአትና በበደል የሞቱትን አስነሳቸውና፡ ዛሬ ማታ፡ ወደ አዲስ ሕይወት አምጣቸው። ኢየሱስን ማየት ይሁንልን። በሰሙ እንለምናለን። አሜን።

7 አረፍ አረፍ በሉ። የመቀመጫ አቅም ባለመኖሩ፡ ሰዎቹን ማስተናገድ ባለመቻላችን እናዝናለን። ነገር ግን፡ ከመጀመሪያው ምሽት ጀምሮ፡ ብዙ ሰዎችን መመለሳቸውን ተናግረዋል፡ ስለዚያም ይቅርታን እንጠይቃለን። ወንድም ግራንት ደግሞ፡ ሌላ የተገነባ ክፍል፡ አላዘጋጀም... ይህን ግድግዳ ወደ ግራ ያስጠገዋል ብዬ አምናለሁ። የተወደደ፡ መልካሙ ወንድም ዛሬ ይህንን እንደ ዓመታዊ እያደረገኩ፡ ወደ ዳላስ፡ ወደ ቤተክርስቲያኑ እንድመላለስ ጠይቆኛል። በሮች በፍጥነት በሚዘጉበት፡ በዚህ ሰዓት፡ እንዲህ ዓይነቱ ታላቅ ግብዣ፡ ከዚያም ይህ ሰው ተመልሼ እንድመጣና፡ ዓመታዊ ጉባኤ እንዲሆን ይፈልጋል። ያንን አደንቃለሁ።

8 ዛሬ ጠዋት ከወንድም ጎርደን ሊንሴይና፡ ከብዙዎቹ ጋር ህብረት አድርጌ ነበር። በቢውሞንት ለሚደረገው ስብሰባ ስፖንሰር የሆነው፡ ወንድም ፒሪ ግሪን፡ ዛሬ ማታ ከኋላዬ ተቀምጧል። ብዙዎችም፡ ጓደኞቻችን፡ ወንድም ዶን እና ባለቤቱ። እዚህ በመኖራቸው በጣም ደስተኞች ነን። ጌታ ይባርካቸው።

9 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ መ... መልዕክቶቼን በተቻለ መጠን ቀላል ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡ ስለዚህ ልጅ እንኳ ሊረዳቸው ይችላል።

10 ነገ ከሰዓት በኋላ የወንጌል አገልግሎት ነው፡ ሁላችሁም ብትመጡ ደስ ይለኛል።

11 አሁን በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ አገልግሎት ካላችሁ፡ ለምን፡ ባ—— ባላችሁበት ቦታ——ቆዩ። ማንም ሰው የራሱን ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ፡ እንዲመጣ አንፈልግም... ነገ ከሰዓት በኋላ በቤተ ክርስቲያናችሁ ፕሮግራም ካለ፡ እናንተ ግን ከታመማችሁ እና ለመጸለይ መምጣት ከፈለጋችሁ፡ ስለዚህ ጉዳይ ከፓስተራችሁ ጋር ተነጋገሩ፡ ስለዚህ መጥፎ ነገር አያስብም፡ ታውቃላችሁ። እዚህ በዳላስ እና በዙሪያው የሚኖሩትን፡ የ——የኢየሱስ ክርስቶስን አካል በሙሉ ለመርዳት በትብብር እዚህ እንደሆንን አሳውቁት።

12 ስለዚህ፡ ነገ ከሰዓት በኋላ፡ ሁለት-ተኩል ላይ፡ ይመስለኛል፡ የወንጌል መልእክት እሰብካለሁ። ከዚያም ለታመሙ ሰዎች ሁሉ እንጸልያለን፡ በሳምንቱ ውስጥ የተረፉትን የጸሎት ካርዶች እና ነገሮች ሁሉ እንሰበስባለንና፡ ነገ ለሁሉም እንጸልያለን።

13 አሁን የዛሬው ምሽት ርዕሴ ትንሽ እንደ ድራማ ነው፡ ለጥቂት ጊዜ ብቻ እናገራለሁ። ዛሬ ማታ በተቻለኝ መጠን፡ ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ እሞክራለሁ። ምንባቤ፡ "አይዞአችሁ አትፍሩ፡ እኔ ነኝ፡" ኢየሱስ ነው እንዲህ ሲል የተናገረው ሲሆን። ርዕሴም፡ **የባሕሩ ላይ ምስክርነት** የሚል ነው።

14 ይህ የሆነው ከሰዓት በኋላ ከጨለመ በኋላ ሳይሆን አይቀርም፡ ይህ ሲሆን ጸሀይ እየጠለቀች እንደነበረች ሳይሆን አይቀርም፡ ቀኑም አሁን እዚህ እንዳለ ሞቃት ቀን የነበረ ይመስለኛል።

15 የአየር ማቀዝቀዣው ተበላሽቷል፡ እየጠገኑት ይገኛሉ። ለዚያም ነው ልናገር የነበርኩትን፡ ርዕሴን የቀየርኩት፡ ስለዚህ መፍጠን እችላለሁ፡ እናንተም በዚህ ሙቀት ውስጥ መቀመጥ የለባችሁም።

16 ይህ ትልቅ ዓሣ አጥማጅ፡ ቀኑን ሙሉ ያየውን ሁሉ ካየ በኋላ፡ ኢየሱስን በታላቁ አገልግሎቱ ይመለከተው ነበር።

17 እርሱን ለመከተል፡ በዚያን ጊዜ ኖሬ ብሆን ኖሮ ደስ ይለኛ ነበር። ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ አሁንም ተመሳሳይ ነገር የማድረግ ዕድል አለኝ፡ ነገሮችን ሲያደርግ እመለከታቸዋለሁና። በዛሬው ጊዜ እሱን መመልከት ከድሮው ይልቅ እጅግ ይበልጣልና። አሁን በእሱ ላይ የበለጠ እምነት አለኝ፡ ያን ጊዜ ከነበረኝ የበለጠ እምነት አሁን ሊኖረኝ ይችላል፡ ምክንያቱም ወንጌሉ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሁለት ሺህ ዓመታት አግኝተናል። ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላም፡ እርሱ አሁንም ህያው ነው፡ በዚያን ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ይሠራል፡ ስለዚህ ከዚያ በፊት ከነበሩት ይልቅ አሁን የበለጠ ዋስትና እና ለእምነታችን የበለጠ መሠረት አለን።

18 ምክንያቱም፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ እና ከእግዚአብሔር ስለመላኩ እየተናገረ የ—የሚዞር ሰው ብቻ ነበር፡ እግዚአብሔርም የዘመኑን ቃል፡ በእሱ ያረጋግጥ ነበር፡ ሌሎች ያንን የሚያጠራጥራቸው ትንሽ ምክንያት ነበራቸው። የሃይማኖት ምሁራኖች፡ ነበሩ! ያም አሳዛኝ ነገር እንደነበረ አስተውላችኋል፡ በእውነቱ አሳዛኝ ነበር፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓይኖቻቸውን ባያሳውር ኖሮ የሃይማኖት ሊቃውንት ያምኑ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዛ ብሏልና።

19 ዛሬም እንደገና እንዳየኸው፡ ዓይኖቻቸውን እንደሚያሳውር ቃል እንደገባ ታውቃላችሁ? ሰዎች "ትዕቢተኞች፡ ዕብሪተኞች፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡ ዕርቅን የማይሰሙ፡ ሐሰተኛ ከሳሾች፡ ራሳቸውን የማይገዙ፡ መልካም የሆነውን የማይወዱ ይሆናሉ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ሃይሉን ግን ክደዋል።" በትክክል ቃልኪዳኑ በድጋሚ መጣ። ለሰዎቹም አለማዘን አይቻልም፡ ዓይኖቻቸውም እስከዛሬ ድረስ ታውረዋልና። በቅዱሳት መጻሕፍት አማካኝነት እግዚአብሔር ቃል የገባው ነገር በዚህ ዘመን፡ በዚህ ሰዓት እየተፈጸመ ነው፡ እኛም ይህን እያየን እንገኛለን። ከዚያም ሰዎች ይመለከቱና፡ ጭንቅላታቸውን አነቃንቀው፡ "አይታየኝም፡" ብለው፡ ይሄዳሉ። ይህ አሳዛኝ ነገር ነው፡ ሆኖም ቅዱሳን መጻሕፍት መፈጸም አለባቸው። ግዴታ በዚህ መንገድ መሆን አለበት።

20 ስለዚህ እነዚህ ደቀ መዛሙርት በእግዚአብሔር የተመረጡ ነበሩ። ኢየሱስ እንደተናገረው፡ "ዓለም ከመመስረቱ በፊት፡" እግዚአብሔር እንደመረጣቸው፡ አስተውላችኋል፡ የተሾሙ የእግዚአብሔር ዘሮች ነበሩ። ለዚህም ነው ችግሮች ሲፈጠሩ፡ ሕዝቡ ኢየሱስን፡ በጥያቄ አንድ ጥግ ላይ ሲያስቸግሩት፡ በእነርሱ ዘንድ ምንም ጥያቄ አልነበራቸውም። ይህን ሊረዱት ባይችሉም፡ ከእሱ በቀር ሌላ ነገር ላለማወቅ ቆርጠው ነበር። "የሕይወት ቃል ያለህ አንተ ብቻ ነህ።" ለዚያም አገልግሎት ስለተሾሙ፡ ከሱ ጋር ለመቆየት ቆርጠዋል።

21 ዛሬም ቢሆን፡ ለዘላለማዊ ሕይወት የተሾሙ፡ ወንዶችና ሴቶች፡ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ይመጣሉ። "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።" ያ ቃሉ

ነው፡ ሊወድቅ አይችልም። የ—የእግዚአብሔር ቃል ነውና።

22 እና ደቀ መዛሙርት አሁን እንደምናያቸው፡ በዚያን ቀን፡ በተራራው ጥግ በሚገኘው ሰፊ ሜዳ ታላቅ ስብሰባ አደረጉ። ኢየሱስም፡ “አሁን ወደ ባሕሩ ማዶ፡ ከእኔ ቀድማችሁ ሂዱ” አላቸው። ኢየሱስም ለመጸለይ፡ ብቻውን፡ ወደ ተራራ ወጣ። እነዚህ ደቀ መዛሙርት፡ ውዳጆቻቸውን ከተገኖኙ በኋላ፡ ምን እንደተሰማቸው እገምታለሁ።

23 ምክንያቱም፡ ከወዳጆች ጋር ተገናኝተህ፡ ከዚያም ከወዳጆች መለየት ማለት፡ ልክ እንደምትለያዩ በምታወቁበት ጊዜ፡ ከዚያ ደህና-ቆዩ ማለት አለባችሁ። በመላ አገሪቱ፡ በዓለም ዙሪያ፡ ወዳጆችን ከተገናኘሁ በኋላ የልብ ህመም የሚሆንብኝ ይህ ነው፡ ወዳጆችን እግኛቼ ስለያቸው ኖሬአለሁና፡ በፍርድ ፊት እስክታገኟቸው ድረስ ከዚያ በፊት መቼም የማታገኟቸው ብዙዎች እንዳሉ ታውቃላችሁና። እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው።

24 ጀልባዋ በባህሩ ውስጥ ስትገፋ፡ በ—በምናቤ መሳል እችላለሁ። እንዲሁም ጀልባዋን እየገፋ ወደ ባሕሩ የቀዘፉት፡ ባለ ፈርጣማ ትከሻዎች እና ክንዶች፡ ስምዖን ጴጥሮስ ሳይሆን አይቀርም። በባህር አጠገብ ለነበሩ ሰዎች ቻው-በማለት እጆቻቸውን ሳያወዛውዙ አይቀሩም። እነሱም፡ “ደግማችሁ ኑ መምህሩንም እንድያየን አምጡልን! ሌላ ጊዜም እንዲህ አይነት ሪቫይቫል አድርጉ፡ ዛሬ በጣም ተባርከናል” እያሉ ይጮኹ ነበር! አዳዲስ ጓደኞችም እጃቸውን ያውለበልባሉ። ወደ ደቀ መዛሙርት ወደ ጀልባው ወጣና፡ ምናልባትም ከወንድሙ ከእንድርያስ፡ አጠገብ ተቀመጠ፡ መቅዘፊያዎቹንም አነሣ።

25 በ—በዚያን ጊዜ መርከቦች የሚንቀሳቀሱት በነፋስ አሊያም በሚጎትቱት መቅዘፊያዎች ነበር። ከዚያም ምናልባት በጀልባዋ ሁለት፡ ሁለት በጎን፡ ወይም… ሁለት በአንድ መቀመጫ ተቀምጠው፡ ይልቁንም፡ ምናልባት ስድስት ወይም ስምንት የመቅዘፊያ ማሰሪያ ነበራቸው። እነሱ በወቅቱ ይጎትቱ ነበር፡ እናም በዚህ መንገድ ዓውሎ ነፋሱ በሚነሳበት ጊዜ ጀልባውን በማሰሪያው መያዝ ይችላሉ። ከዚያም፡ ነፋሱ በተለመደው ሁኔታ ሲነፍስ፡ ከፊት የሚወጠረውን ሸራ ከፍ አድርገው፡ መጓዝ ይችላሉ።

26 ይህ አጋጣሚ ከመፈጸሙ በፊት የነበረው፡ የከሰዓቱ የአየር ጸባይ ሞቃታማ ሳይሆን አይቀርም፡ ስለዚህም ጸጥታ የሰፈነበት፡ ፀሐያማ፡ ሞቃታማ ከሰአት ነበር። ፀሐይ እየጠለቀች ነበር። እነርሱም፡ መቅዘፍ ሲጀምሩ፡ ለቀቅ አደረጉና እጃቸውን እያውለበለቡ ህዝቡን ደህና-ቆዩ አሉ፡ ወደ ባሕሩ ጉዞ እንደ ጀመሩ “የሆነ ጊዜ እንደገና እንደምንገናኝ ተስፋ እናደርጋለን፡” አሉ። ጸሃይም ጠለቀች፡ የምሽት ድንግዝግዝ ሆነ፡ ከዚያ በ—በኋላ ጨለመ።

27 ግዴታ በ—በፍጥነት መቅዘፍ አለባቸው፡ ትላልቅ እና ከባባድ መቅዘፊያዎች ወደ ባሕሩ ጥልቅ ሲወርዱ መቅዘፍ ከባድ ሥራ ነው። አብዛኞቹ ዓሣ አ—አጥማጆችና፡ በባሕር ላይ ልምድ የነበራቸው፡ ጠንካሮች ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስም ወደ ጀልባው ገብቶ በቅርቡ፡ ይከተላቸዋል ብለው ጠብቀውት ነበር። ይሁን እንጂ፡ ወደ ባህር ውስጥ ገብተው፡ ትንሽ ራቅ ብለው ሳይገቡ አልቀሩም፥ መርከቡዋን ማስጀመር፡ ከዚያም በራሷ እንድትሄድ መተው ማለት ነው።

28 ምናልባትም ወጣቱ ዮሐንስ በቡድኑ ውስጥ ታናሽ ስለነበር፡ መጀመሪያ የተናገረው እሱ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ያለው እሱ መሆን አለበት፡ “እኔ እየደከመኝ ነው። እስቲ ለጥቂት ጊዜ መርከቧን እናቀዝቅዛት። እንረጋጋ፡ መቸኮል የለብንም። እሱም ገና አልመጣም፡ ስለዚህ ትንሽ ጊዜ እየጠበቅነው ትንፋሻችንን በደንብ መሰብሰብ እንችላለን።”

29 እርሱም ጭንቅላቱን ወደ ታች ዝቅ አድርጎ ትንሽ እንደተቀመጠ፡ የምስክርነቱ ስብሰባው ሳይጀምረው አይቀርም። እኔ መናገር የፈለግኩትም ይህ ነው። ከሁሉም በፊት የተነሳውና እንዲህ ያለው፡ እሱ ሳይሆን አይቀርም፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ሰዎች ምንም ቢናገሩም፡ የቱንም ያህል ላለማመን ቢፈልጉም፡ እኔ ግን ከዛሬ በኋላ፡ አጭበርባሪን እንዳልተከተልን፡ በትክክል አረጋግጫለሁ። የምንከተለው እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አይደለም፡ እግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ዛሬ እሱ ያደረገውን ማንም ሊያደርግ አይችልም። ታውቃላችሁ፡ እነዚያን እንጀራዎችን ተቀብሎና ቆርሶ፡ አምስት ሺህ ህዝብ መመገብ ማለት፡ ያ ለእኔ ከምንም በላይ አስገራሚ ነገር ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ጥርጣሬ ሊኖርብኝ ይችል ነበር፡” አሁን ምስክርነቱን እንደወረደ እየደገምኩት ነው፡ “ይሁን እንጂ ያ አራት ነጥብ ነው።”

30 እንዲህ አለ፡ “ከዓመታት በፊት ትዝ ይለኛል። በዮርዳኖስ ወንዝ አቅራቢያ እኖር ነበር። ትንሽ ልጅ ሳለሁ፡ ቆንጆዋ፡ አይሁዳዊቷ እናቴ፡ ከሰዓት በኋላ ላይ እንዴት እንደምትሸከመኝ፡ አስታውሳለሁ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻዎች፡ አበባዎች በሚበቅሉበት ጊዜ፡ በረንዳ ላይ በእቅፏ አድርጋ ታዝናናኝ ነበር። እና ወገኖቻችን አቋርጠው የመጡበትን ምድረበዳ ፊት ሆና፡ ወደ ምድረበዳው አቅጣጫ ታማትር ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ትነግረኝ ነበር። ከማስታውሳቸው ታላላቅ ታሪኮች መካከል አንዱ፡ ሱናማዊት ሴት ነበርችና ትንሹ ልጇ በሞተ ጊዜ፡ ነቢዩም እንደገና ከ—ከሙታን ይህን ትንሽ ልጅ አስነሣው። ያ በጣም አስደሳች ታሪክ ነበር።

31 “ነገር ግን በጣም ከአስደሳች ታሪኮች መካከል አንዱና፡ እናቴ ትነግረኝ የነበረው፡ እንዲህ ትነግረኝ ነበር፡ ‘አሁን፡ ዮሐንስ፡ አንተ ገና ትንሽ ልጅ ነህ፣ ነገር ግን እያደግህ ስትሄድ፡ እንድታስታውስ የምፈልገው፡ ያ፡ ታላቁ እግዚአብሔር ሕዝባችንን ከግብፅ አወጣ፡ በዚያም ወንዝ አቋርጠን በዚያ ምድረ በዳ መጣን። ለአርባ ዓመታት፡ በምድረ በዳ ሲጓዙም፡ ልብስ የሚለብሱበትና፡ የሚበሉበት ቦታ አልነበራቸውም። እግዚአብሔርም በየምሽቱ፡ ከሰማይ እንጀራ አዘነበ፡ ሕዝባችንንም በዚያ ምድረ በዳ መገበ፡ ምክንያቱም በታላቁ እግዚአብሔር ሥር በመሆን፡ ታማኝ አገልጋዮቹ ነበሩ። አሁንም ደግሞ፡ አንድ ቀን፡ ያህዌ ሰው ሆኖ በምድር ላይ ሥጋ ለብሶ፡ በሰው መልክ ይመጣል፡ የተቀባ፡ ወይም መሢሑ ተብሎ ይጠራል።’

32 “አስታውሳለሁ፡” እንዲህ ይላል፡ “ትንሽ ልጅ ሳለሁ፡ ያንን ነገር ለመረዳት፡ በትንሿ አእምሮዬ እጅግ አውጠነጥን ነበር፡ ‘እግዚአብሔር እነዚያን ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ሰዎች፡ በምድረበዳው ውስጥ፡ እንዴት ሊመግባቸው ቻለ? ያ ሁሉ እንጀራስ ከወዴት አገኘ?’ እናቴንም እጠይቃት ነበር፡ ‘እማዬ፡ ያህዌ፡ በ—በሰማይ ላይ ብዙ ምድጃዎች ስለነበሩት ነው፡ እንጀራውን ሁሉ ጋግሮ፡ በሌሊት ሮጦ ለ—ለሕዝቡ መሬት ላይ፡ ይጥልላቸው የነበረው፡ የያህዌ ታላላቅ ሰማያት በምድጃዎች የተሞሉ ነበሩን?’ እሷም እንዲህ ትለኝ ነበር፡

“አይ፡ ልጄ፡ ይህን ለመረዳት አንተ ገና ልጅ ነህ። አየህ፡ ያህዌ ፈጣሪ ነው። ምድጃዎች አያስፈልጉትም። እርሱ ይናገራል፡ እርሱ ሲናገርም ቃሉ ይገለጣል። እርሱ ታላቁ ያህዌ ነው፡ በቃሉ ብቻ ተናገረ። መላእክትም በምድር ላይ፡ ለሰዎች አከፋፈሉት።’

33 “ዛሬም፡ በዚያ ቆሞ ሳየው፡ የፊቱን ገጽታ አስተውላችኋል? በአእምሮው ውስጥ ምንም ጥርጣሬ አልነበረም። እንጀራውን ወስዶ ሲቆርሰውና፡ እንዲያከፋፍሉትም፡ ለአገልጋዮች… ማለትም ለእኛ፡ ለሕዝቡ እንድናከፋፍል ሲሰጠን፡ ተመለከትኩት። ከዚያም ዳግመኛ ለመቁረስ ወደ ኋላ ሲመለስ፡ ያ እንጀራ እንደገና ሙሉ ሆነ። ይህንንም ሁሉም ሰው እስኪጠግብ ድረስና፡ መሉ፡ መሶቦች፡ እስኪነሱ ድረስ፡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ጊዜያት አደረገ። ያህዌ እንዳደረገው ሰላደረገ፡ ይህ ከያህዌ ያነሰ ሊሆን እንደማይችል አውቄአለሁ። መፍጠር የሚችለው ያህዌ ብቻ ነው። ያ ሰው ሐሰተኛ እንዳልሆነ አውቃለሁ። ፈጣሪ አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም ያህዌ ነው። አሁንም፡ ካየኋቸው ነገሮች ሁሉ፡ ይህ አርክቶኛል።

34 “አሁን ልቤን ሙሉ በሙሉ አሳልፌ እንደሰጠሁ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፡ እርሱም ነቢይ ብቻ እንዳልሆነ ሙሉ በሙሉ አምናለሁ። አዎን ነቢይ ነው፡ ከነቢይም የሚበልጥ ነው። እርሱ በመካከላችን ተገልጦ የሚኖር ያህዌ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሌላ አይደለም፡ እንጀራንም ፈጥሯልና፡ የያህዌ ልምምድ አለውና። እንዲህ ብሎ መናገሩም አያስገርምም፡ ‘የአባቴን ሥራ የማልሰራ ከሆነ፡ አትመኑኝ፣ የአባቴን ሥራ እየሰራሁ ከሆነና፡ ልታምኑኝ ካልቻላችሁ ግን፡ ሰለ እኔ የሚመሰክሩትና፡ እኔ ማን እንደሆንኩ የሚናገሩትን ሥራዎች እመኑ።” ሰዎች በቀላሉ፡ ሊያዩት የሚችሉት ይመስላል።”

35 ዮሐንስም እርሱ መሲሕ መሆኑንና፡ ኢሳይያስም ሰለ እርሱ የተናገረለት እርሱ እንደሆነ አረጋግጧል፡ “ወንድ ልጅ ተወልዶልናልና፡ ሰሙም መካር፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ይባላል።” ዮሐንስም ባየው ነገር ረካ። ወጣቱም ምስክርነቱን ሰጠ።

36 በዚያን ጊዜ፡ ሰምዖን ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡ “መልካም፡ አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። የምስክርነት ጊዜ የምናደርግ ከሆነ፡ አንድ ነገር መናገር እፈልጋለው። ታውቃላችሁ፡ ወንድሜ እንድርያስ የመሲሑ መምጣት፡ እንደሚያስተዋውቅ የተናገረውን፡ የነቢዩ የዮሐንስን ሪቫይቫል በተከታተለ ጊዜ፡ እኔ በሁሉም ነገር እጅግ በጣም ተጠራጣሪ ነበርኩ። እንድርያስም ሰለሚነግረኝ ነገር ትንሽ ተጠራጥሬው ነበር፡ ምክንያቱም የመሲሑን ሁሉም አይነት ታሪኮችና ሌሎች ነገሮችም ሰምቻለሁና።

37 “ነገር ግን ወንድሞቼ ሁላችሁም አባቴን ታስታውሱታላችሁ። ሰሙ ዮናስ ነበር። እንዴት ጠንካራ አማኝ እንደነበረ፡ ታስታውሳላችሁ። እናቴንና አባቴን፡ ሁላችንንም አስታውሳለሁ፡ ኑሮን ለመግፋት አሳ ሰናሰግር፡ የሚጠመድ አሳ አጣን፡ እንጀራ ያስፈልገን ነበርና፡ ወደ መሬት ወርደን ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ ነበር፡ ‘እግዚአብሔር ሆይ፡ ዓሣችንን ለመሸጥ እንድንችል፡ እዳዎቻችንንም ለመክፈል እንድንችል፡ የምንበላው ምግብ እንዲኖረን፡ ዛሬ ዓሣ መግፈፍ እንድንችል እርዳን።’ ያን ጊዜ ወደ ባሕር እንሄዳለን፡ በዓውሎ ነፋሱ ውስጥ፡ እነዚያን ዐውሎ ነፋሶችን ለ—ለመጋፈጥ እንደደፍር ነበር።

38 “አባቴም፡ ሽበታም ፀጉሩ ጀርባው ላይ ተንጠልጥሎ፡ አንድ ቀን በጀልባው ላይ ተቀምጦ ሲያነጋግረኝ አስታውሳለሁ፡ እንዲህ ሲለኝ፡ ‘ስምዖን ሆይ፡ አንተ በኩር ልጄ ነህ። ታውቃለህ፡ ስምዖን፡ መሲሑን እያለሁ ብዬ፡ እያመንኩ ኖሬአለሁ። ወገኖቻችንም ከዔደን ገነት ጀምረው ሲጠብቁት ቆይቷል። ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅም፡ እንደሚመጣ እርግጠኞች ነን። አራት ሺህ ዓመታት ሆኖታል፡ ማለት ትችላለህ። እኔ ግን መሢሑ እንደሚመጣ አምናለሁ። እያንዳንዱም አይሁዳዊ በትውልዱ ውስጥ መሲሑን እንደሚያየው ያምናል። እኔም በትውልዴ እሱን ለማየት ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ግን፡ እያረጀሁ እንደሆነ ይሰማኛል፡ ወደዚህ ባሕር መምጣትም አቆማለሁ፡ እያመመኝና እየደከመኝ ነው፡ ምናልባት በዘመኔ አላየውም ይሆናል። ምናልባት አንተ ታያለህ፡ ልጄ።

39 “‘እንዲሁም በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ ላስተምርህ እፈልጋለሁ። ልጄ ሆይ፡ መሢሑ ከመምጣቱ በፊት፡ የተለያዩ ነገሮች ይሆናሉ፡ የተለያዩ ሐሰተኛ ነገሮች ይሆናሉ፡ ምክንያቱም ሰይጣን ይህን የሚያደርገው፡ እውነተኛው መሢሕ በሚመጣበት ጊዜ ተፅዕኖውን ለማጥፋት ነው።’” ሁልጊዜም እንደዚያ ነበር፥ አሁንም እንደዚያ ነው።

40 በዚያም እናውቃለን፡ እንዲህ አለኝ፡ “ክንዶቹን በእኔ ላይ ጣል ሲያደርግ አስታውሳለሁ፡ እንዲህ አለኝ፡ ‘ልጄ ሆይ፡ ያንን መሢሕ መለየት የምትችልበት አንድ መንገድ ብቻ አለ። አሁን ያለ አንዳች ነቢይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታትን አሳልፈናል። የመጨረሻው ነቢያችን ሚልክያስ ነበር። ይህ የሆነው ከአራት መቶ ዓመታት በፊት ነው፡ ነቢይ አልነበረንም። ነገር ግን፡ ሙሴ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ መሢሑ ሲመጣ፡ በጊዜው ሲመጣ፡ ነቢይ ይሆናል ብሎ፡ እንደነገረን አስታውስ። እኛ አይሁዶች ነብይን ማመን እንዳለብን ተምረናል። የመሲሁም ህይወት በምድር ላይ ቃል የገባልን፡ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉ ሁሌም ወደ ነቢይ ይመጣል፡ ነቢይም ቃሉን ያረጋግጣል። ልጄ ሆይ፡ ይህን ፈጽመህ አትርሳ! ታላላቅ ነገሮች ሊነሱ ይችላሉ፡ ታላላቅ ጉጉቶች እና ታላላቅ ነገሮች—ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን አስታውስ፡ መሰሑ ነቢይ እንደሚሆን አስታውስ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንገዱን እንደማይለውጥ እናውቃለን፡ መሲሑም ነቢይ እንደሚሆን ተናግሯል። ስለዚህ ልጄ ሆይ፡ ነቢያት የጌታን ቃል የያዙ ሰዎች መሆናቸውን፡ አስታውስ። መሢሑ ሲመጣም፡ ነቢይ ይሆናል።’

41 “ያቀፈኝ እጁ እስከ አሁን ድረስ ይሰማኛል፡” ስምዖን አለኝ፡ “እጁን በእኔ ላይ እንዳደረገ። በስኣቱ፡ እንድርያስ ቆሞ መረቡን እያጠበ ነበር። ታስታውሳለህ፡ እንድርያስ? ”

“አዎን፡ ስምዖን፡ አ—አስታውሳለሁ።”

42 “እንድርያስም ይህ ዮሐንስ ነቢይ ነው እያለ ይነግረኝ ነበር። ማድረግ ያለብኝ ሌሎች ነገሮች ነበሩኝ፡ ዓሣ እና ነገሮች መሸጥ ነበረብኝ። እንግዲህ አባቴ ከሞተ ቆይቷል፡ ያ ግን ሁልጊዜ በአምሮዬ ውስጥ ጠብቄአለሁ፥ አባቴ እንዲህ አለኝ፡ ‘መሢሑ በቅዱሳት መጻሕፍት የሚታወቅ ነብይ ይሆናል፡ እርሱ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚሆን፡ ፈጽመህ እንዳትረሳ። ቃልም ለነቢያት ዘወትር ይመጣላቸው ነበር፥ ያ ደግሞ በዚያ ዘመን በተገባው ተስፋ ቃል ይታወቃል፡ ወይም ይገለጣል።’”

43 አሁን ሰምያንም፡ “አንድ ቀን፡” አለ፡ እንዲህ አለ፡ “ታውቃላችሁ፡ እንድርያስ አንድ ጉባኤ እንድሳተፍ ጋበዘኝ። ወርጄም፡ ኢየሱስ የተባለ ሰው፡ ወደነበረበት ጉባኤ ሄድኩ። ከዚያ በፊት ብዙ ዓይነት ወሬዎች ሰምቼ ነበር። ከእሱ በፊት፡ ታላቅ ነኝ እያለ የተነሳ፡ ሌላ ኢየሱስ ተነስቶ ነበር፡ አራት መቶ ሰዎችን መራ፡ ሁሉም ጠፋ ተበታተኑም። ይህም ከእነርሱ እንደ አንዱ ነው ብዬ አሰብኩ፡ ወይም ሊመሰርቱት በነበረው ታላቅ ሃይማኖት ተቋም፡ ወይም የሆነ አይነት ሪቫይቫል ላይ ያው ነው አልኩ። ይሁን እንጂ አንድ ቀን ከወንድሜ ከእንድሪያስ ጋር፡ ለመሄድ አሰብኩ።”

44 ይመስለኛል፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፡ ጀልባዋ መናወጥ ጀማምሯታል። የሆነ ሰው መጮኽ ጀመረ፡ እንዲህ ይላል፡ “ተቀመጡ! ጀልባውን አታወዛውዙ። ቆዩ አንድ ደቂቃ ጠብቁ። እርፋችሁ ተቀመጡ።”

45 እርሱም እንዲህ ማለቱን ቀጠለ፡ “ታውቃላችሁ፡ ወደዚያ ወርጄ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፊቱ ቀረብኩ፡ በቀጥታ ወደ ዓይኔ ተመልክቶ ስሜን ነገረኝ። ከዚህ በፊት አይቶኝ አያውቅም ነበር። የእኔንም ብቻ ሳይሆን፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን ያስተማረኝን መንፈሳዊን አባቴን ጭምር፡ አወቀው። ያን ጊዜ መሢሕ መሆኑን አወቅኩት። ያም ለእኔ፡ አራት ነጥብ ነበር። ያ ነው። ያረጋገጠልኝ፡ ያ ነው።”

46 በመቀጠል የተናገረው ፊልጶስ ነበር እንዲህ በማለት፡ “አንድ ነገር መናገር እችላለሁ? ” አሁን እንዲህ አለ፡ “ወንድም ናትናኤል ሆይ፡ አደራ በዚህ እንዳትሰናከልብኝ፥ ምክንያቱም፡ የመሲሑን ማንነት ለማወቅ ለዓመታትና ዓመታት፡ ብራናዎችን ሰናጠና ኖረናል። ይህን ሲያደርግ ባየሁት ጊዜ ግን፡ ተነሳውና ወዳጄን ናትናኤልን፡ ይዤ መጣሁ። እርሱ ሲመጣ... ”

ናትናኤልም ቀበል አረገና “እኔ ልናገር። እኔ ልናገር፡” አለ።

47 ኦህ፡ ታውቃላችሁ፡ ኢየሱስ የሆነ ነገር ሲያደርግላችሁ የሆነ ነገር ትሆናላችሁ፡ ራሳችሁ—እስከምትናገሩ ድረስ፡ ዝም ብላችሁ፡ መቆየት አትችሉም። ልክ ነው አይደል? እውነተኛ ነገር ከሆነ፡ መናገር አለባችሁ። በመንፈስ ቅዱስ በሞላኝ ጊዜ፡ ስለዚያ መናገር እፈልጋለሁ። አንድ ሰው እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ። ሌላ ሰው ሳይሆን፥ ራሴ፡ መናገር እፈልጋለሁ።

48 ናትናኤል ጓግቶ፡ እንዲህ ሲል ተመልከቱት፡ “ይኸውላችሁ፡ ይህን እኔ ልናገር። ፊልጶስ፡ አንተ ሰትነግረኝ፡ ትንሽ ተጠራጥሬህ ነበር። ‘ከናዝሬት መልካም ነገር ሊመጣ ይችላልን፡’ ብዬ ጠየቅኩህ? ‘አንተም ናና እይ፡’ የሚል በጣም ጥሩ መልስ ሰጠኸኝ።” ይህም ለዛሬ ጥሩ መፍትሔ ነው። በትክክል። ቤት ውስጥ ሆናችሁ አትተቹ። ኑና፡ ራሳችሁ እይታችሁ እወቁ፡ እያችሁ። “እንዲህ አለ፡ ‘ከናዝሬት ጥሩ ነገር ሊወጣ ይችላልን? ’ እንዲህ አለ፡ ‘ናና ራስህ እይ።’ የነገርከኝን ታውቃለህ።

49 “ወደ እርሱ ፊት በወጣሁ ጊዜ፡ ‘ዕ—ዕብራዊ ሰው መሆኔን፡ እስራኤላዊና፡ እውነተኛ ሰው ነህ’ አለኝ፡ አውቃልሁ።

50 “እኔ ግን እንዲህ ስል ራሴን ጠየቅኩ፡ ‘እንዴት ሊሆን ይችላል? ’ ተራ ሰው ይመስላል። መሢሑ ከሰማይ በወርቃማ ኮሪደሮች ይወርዳል ብዬ ስጠባበቅ ኖሬአለሁ፡ በቀጥታ ወደዚህ ወደ ሃይማኖት ተቋም ጣራ፡ ወደ ኢየሩሳሌም፡ ይወርድና፡ ጎርደድ ጎርደድ እያለ ‘ቀያፋ ሆይ፡ እነሆ ደርሻለሁ’ ይላል ብዬ

ስጠብቅ ኖርኩ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ የመጣው ከናዝሬት እንደሆነና፡ ድሀ ከሆነ ቤተሰብ፡ እንደሆነ ተገነዘቡ፥ በእውነቱ ከበስተጀርባው ‘ዲቃላ፡’ የሚል የስድብ ስም ሰጥተውት ነበር። እነሆ እርሱ፡ ተራ ልብስ ለብሶ ነበር፡ እንደ ካህን ወይም እንደ ሌላ ሰው ሳይሆን፥ ተራ ሰው ነበር። ወደዚያም በደረስኩ ጊዜ፡ እንዲህ አልኩ፡ ‘ይህ እንዴት መሢሕ ሊሆን ይችላል? የነተበ ልብስ የለበሰ፡ ከወጣትነት ጀምሮ የለበሰውን፡ ያንኑን እንደለበሰ ነው፥ ፀጉሩ በጀርባው ላይ ወድቋል። እንደ ተራ የጎዳና ሰው ይመስል ነበር።’

51 “ፊቴን ተመለከተኝና፡ ‘ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ በዛፉ ሥር ሳለህ፡ አየሁህ፡’ አለኝ። ያ ለኔ እራት ነጥቤ ነበር። እርሱ መሢሕ መሆኑን፡ ከቃሉ፡ አውቄያለሁ። ያ እርሱ ነበር።”

52 የምስክርነት ስብሰባው እንደቀጠለ፡ ጀልባዋ ሳትናወጥ አልቀረችም። ኦህ፡ በባሕር ላይ ምን አይነት፡ አስደናቂ ጊዜ እያሳለፉ ነበር፡ ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ ነበር።

53 እንድርያስ እንዲህ አለ፡ “ለጥቂት ጊዜ ግራ ያጋባኝን አንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። ወደ ኢያሪኮ ስንወርድ የ—የነበረውን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? ‘ወደ ላይ እንውጣ፥ በሰማርያ በኩል ማለፍ አለብኝ፡’ አለን። ስለዚህ፡ ወደ ሰማርያ ወጥቶ በዚያም በሲካር ከተማ በነበረበት ጊዜ፡ በከተማው ውስጥ ምግብ እንድንገዛ ሁላችንንም አሰናበተን።”

54 “ኦህ፡ አዎ፡ በደምብ፡ አስታውሳለሁ!” ሁሉም፡ “አዎን፡ አዎን!” ሪቫይቫሉ ካለቀ በኋላ ሁሉም በአንድነት ድንቅ የምስክርነት ጊዜ እያሳለፉ ሳሉ፡ ጀልባዋ መንቀጥቀጥ ጀመረች። ስለዚህ ይህ የምስክርነት ጊዜ እያደረጉ ነበር።

55 እርሱም፡ “አዎ፡ ሁላችንም ሰተን እንደነበር ታስታውሳላችሁ፡ ያስገረመን ነገር፡ ጌታችን ከታወቀች፡ ሴተኛ አዳሪ ጋር ሲነጋገር አየነው። ‘አይ-ሃህ፡’ እንዲህ አሰብን፡ ‘መጥፎ ነገር ነው። ተመልከቱት ከዚች ወጣት ሴት ጋር እየተነጋገረ ነው። እኛን ሌላ ቦታ ልኮ፡ እዚህም መጥፎ-ሰም ካላት ሴት ጋር ተቀምጧል።’ ከቋትቋጦ በስተጀርባ ቆመን፡ ውይይታቸውን ሰናዳምጥ እንደነበር፡ አስታውሱ።

56 “እርሱም፡ ‘አንቺ ሴት፡ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነይ‘ ሲላት ሰማነው።

57 “ከዚያም እንዲህ አልን፡ ‘መልካም፡ ተሳስተን ሊሆን ይችላል፡ ምናልባት ሴቲቱ በህጋዊ መንገድ ትዳር አላት።’

58 “ሴቲቱም መልሳ ፊቱን ተመለከተችና፡ ‘ባል የለኝም፡ ጌታዬ፡’ አለችው።

59 “ልባችን እንዴት እንደወረደ ታስታውሳላችሁ? የተማመንንበት ታላቁ መሲሃችን፡ በውሸት ተያዘ፡ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ፡ ምክንያቱም ‘ሂጅና ባልሽን ጥሪው፡’ አላት፡ እሷም ባል እንደሌላት መልሳ መሰከረች። ከባድ መልስ ተመለሰለት። ሁላችንም እንዴት እንደተደነቅንና፡ ትንፋሻችን እንዴት ከውስጣችን እንደጠፋ ታስታውሳላችሁ? ”

“አዎን፡ እኔ አስታውሳለሁ።”

60 “ከዚያም ቀጣዩን ቃል ታስታውሳላችሁ? እንዲህ አላት፡ ‘የተናገርሽው እውነት ነው፡ ምክንያቱም አምስት ባሎች ነበሩሽ፡ አሁን አብረሽው የምትኖሪው ባልሽ አይደለም።’ ኦህ፡ ከቊጥቋጦው በስተጀርባ የነበረ የምስክርነት

ሰብሰባ ታስታውሳላችሁ? ማይ!" እያችሁ፡ እርሱን ማሸነፍ አትችሉም። እርሱ እግዚአብሔር ነው። ስምዖን "ኦህ፡" አለ፡ "በቃ በቂ ነው... " እንድርያሰም "ያ ለእኔ አራት ነጥብ ነው፡" አለ።

61 በርቴሎሜዋሰም አለ፡ "ቆይ፡ ምስክርነት መሰጠት እፈልጋለሁ። መመሰከር እችላለው፡ ወንድሞቼ? "

62 "ኦህ፡ መልካም፡ ኧረ ትችላለህ፡ በቂ ጊዜ አለን። እሱም ገና አልመጣም፡ ትንሽ እንቀዝፋለን። ቀጥል፡ በርቴሌሜዋሰ፡ መሰክር።"

63 "መልካም፡ ለእኔ ከታላላቅ ነገሮች አንዱ፡ ርብቃ የተባለች ኢያሪኮ የምትኖረውን፡ እህታችንን ታስታውሷታላችሁ? "

"እዎን።"

"ባለቤቷም እዚያ ምግብ ቤት አለው።"

"እህ-ሃህ።"

64 "እና—ነጋዴ ነበር፡ ሰሙም ዘኬዎሰ ይባላል።"

"እዎን፡ አዎን፡ በደንብ አስታወስኩት።"

65 "እሷን ታስታውሳላችሁ፡ ከ—ከእህቶቻችን አንዷ ነበረች። በጌታ አምና ነበር፡ ዘኬዎሰም ኢየሱሰን ሳይቀበል እንዳይኖር በጣም ፈርታ ነበር። ደግሞም፡ ኦህ፡ ዘኬዎሰ የዚያ የካህኑ ጥሩ ወዳጅ ነበር። ሰለዚህም የሆነ ነገር እንዲሆን እየጸለየች ነበር ዓይኖቹ እንዲከፈቱ፡ መምህር መሆኑን፡ የተረጋገጠ የእግዚአብሔር ቃል በመካከላችን ሥጋ እንደሆነ፡ እንዲገነዘብ ሰትጸልይለት ነበር። እኛም የ... የናዝሬቱ ኢየሱሰ የልብን ምሥጢር እንዴት እንደሚያውቅ ልንነግረው እየሞከርን ነበር፡ ቃል በልብ ውሰጥ የተሰወሩትን ሃሳቦችን ይለያልና፡ እርሱ ቃል መሆኑን ለማሳየት ሞከርን።

66 "እርሱም 'ይህ ከንቱነት ነው፡' አለ፡ 'ቄሱን እምናለሁ። ቄሱ የሚናገረው ነገር ለእኔ በቂ ነው' አለ። ምክንያቱ በከተማዋ እሉ የተባሉ ማሕበረሰበቦች አባል ነው፡ የነ ኪዋኒሰ እና የሌሎች፡ ነገሮች፡ ሰ... ሰለዚህ ያን ለመተው ከባድ ነበር። ሰለዚህ ርብቃ ሁላችን—እንድንጸልይ ጠየቀችን። እርሱ ነቢይ ነው የሚለውን ርዕሰ ካነሳንበት፡ እንዲህ ይል ነበር፡ ይህ 'ከንቱነት ነው! ካህኑም፡ "እሱ'ኮ ብዔል ዜቡል ነው፡ ዲያብሎሰ ነው። ይህን የሚያደርገው በዲያብሎሰ ኃይል ነው። የአዕምሮ ቴሌፓቲሰት ብቻ ነው። ያ ነው። ምንም ነገር የለውም" ይል ነበር። ዛሬ እንዲህ ያለ ነገር የለም፡ በመቶዎች ለሚቈጠሩ ዓመታት ነቢያት አልነበሩንም። ይህ ሰው፡ የአባልነት መታወቂያ ካርድ እንኳ ሳይኖረው፡ እንዴት ነቢይ ሊሆን ይችላል? ኦህ፡ አይሆንም እርሱ ተራ ነገር ነው!'

67 "ታውቃላችሁ፡ ርብቃ፡ ሚሰቱ ግን፡ ጸሎት ማድረግን፡ ቀጠለች። አንድ ቀን ጠዋት ኢየሱሰ ወደ ከተማው ሲመጣ፡ ያን ጊዜ፡ ርብቃ እንደነገረችን፡ ዘኬዎሰ እሱን ለ—ለማየት ወደ ጐዳና እንደወጣ፡ ነገረችን። ሰለዚህ ነቢይ መሆኑን ሳያምን፡ እንዲሁ እንዲህ አለ፡ 'ብቻ በደምብ ልመልከተው፡' ባለፈው ቀን ምግብ እየበላን በነበርንበት በዚያ ምግብ ቤት መሰክሮልን ነበር። ሰለዚህ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፡ እንዲህም አለ፡ 'ይኸውላችሁ፡ እንዳያውቀኝ አድርጌ ሌላ ሰው እመሰላለሁ። ሲጀመርም'ኮ፡ አጭር ነኝ፡ በጣም አጭር ነኝ። በሕዝብ ውሰጥ፡ እሱን ማየት አልችልም፡ ሰለዚህ ዛፍ ላይ እወጣለሁ።' መ—

መንታ ቅርንጫፎች ወደሚገናኙበት ዛፍ ወጣና፡ በዚያም በቅርንጫፎች ላይም፡ ተቀመጠ።"

68 ቁጭ ብሎ ለማጥናት ምቹ ቦታ ነበር። የእናንተና የእግዚአብሔር፡ ሃሳባችሁ፡ የሚገናኙበት ባለ መንታ መንገድ ነው፡፡ እንደገና ለማሰብ የሚጠቅም፡ ጥሩ ነገር ነው፡፡

69 "ስለዚህ እንዲህ አለ፡ 'እንደውም'ኮ፡ ነቢይ ሊሆንም ይችላል። ሊሆንም ይችላል። እኔም ልሳሳት እችል ይሆናል። ስለዚህ ይኸውላችሁ፡ በደምብ እየዋለው፥ እኔን ግን አያውቀኝም። ስለዚህ ቅጠሎቹ እንዲህ ሰቤአቸው፡ በላዬ ላይ እሸፍናቸዋለሁ፡ በጭራሽ እንዳያየኝ እራሴን እደብቃለው። በሚመጣ ጊዜም በደንብ እየዋለው። ትክክለኛ ዓይነት ሰው የማይመስል ከሆነ፡ በዚህ ዛፍ ላይ ቁጭ ብዬ፡ ሃሳቤን በግልጽ እናገራለው።' ስለዚህ ተመለከተው፡ በጥግ ሲያልፍ ከፍ አድርጎ እንዲያየው ቅጠል ይዞ ነበር።

70 "በመንገዱ ጥግ፡ ታውቃላችሁ፡ በመንገድ ከዚኛው ጥግ እስከዚያኛው እየተመለከተ፡ እየተራመደ በሚመጣ ጊዜ፡ ደቀ መዛምርትም እንዲህ ይላሉ፡ 'ይቅርታ አርጉልን። መንገድ ክፈቱ።' የታመሙ ልጆችና ሌላ ነገሮች የያዙ ሰዎች። 'ይቅርታ አርጉልኝ፡ መምህሩ በጣም ደክሞታል፥ ትላንት ማታ ታላቅ አገልግሎት ነበረው።' አንተ፡ ወጣት፡ 'እባክህ እንዲያልፍ መንገዱን ለቀቅ አርግለት፡ ወደ ከተማው እየወረደ ነውና፡ እባካክህ መንገድ ልቀቅለት?' ዘኬዎስ ዛፍ ላይ ተቀምጦ፡ ወደ ታች እሱን ይመለከት ነበር።

71 "ኢየሱስም በቀጥታ ከዛፉ ሥር ደርሶ፡ ቆመ፡ ወደ ላይ ተመለከተና፡ 'ዘኬዎስ፡ ከዚያ ውረድ። ዛሬ እራት ለመብላት፡ ከአንተ ጋር ወደ ቤትህ እሄዳለሁ።' ይህ የነገሩን እልባት ሰጠኝ። እዚያ ላይ እንደነበረ ያውቅ ነበር፡ ስሙ ማን፡ እንደነበረም ያውቅ ነበር። ይህ አረጋገጠ። ያ ለእኔ፡ መሢሕ ነው። አዎ፡ ወዳጄ። ምክንያቱም፡ መሢሕ ያንን እንደሚያደርግ እናውቃለን። በእርግጠኝነት። ስለዚህም በዚያ ቀን፡ እራት ላይ፡ ከእሱ ጋር ወደ ቤት መሄድ እንዳለበት ተናገረ። ምን አይነት ታላቅ ጊዜ ነበር! እናስታውሰዋለን።"

72 ታውቃላችሁ፡ የምስክርነት ሰብሰባው የተደረገው፡ ያን ጊዜ መሆን አለበት። ይኸውላችሁ፡ እነዚያ ደቀ መዛሙርት በባህር ላይ፡ በምስክርነት በነበሩ ጊዜ፡ በዚያ በሰሜናዊው አቅጣጫ፡ ክው ባለው ሌሊት በሆነ ሰፍራ መኖራቸው አይቀሬ ነበር፡ ሰይጣንም ወደ ኮረብታው እናት ላይ ወጥቶ ቁልቁል ሳይመለከታቸው አይቀርም። በዚያ በምስክርነት ሰብሰባቸው ውስጥ ተመለከተና፡ ያለ እርሱ እንደተጓዙ ተገነዘበ። ያኔ ዕድሉ ነበረች።

73 አያችሁ፡ ይህ ትዕይንት እንደገና እንደመጣ እና፡ እራሱን እንደደገመ አሰባለሁ። ያን ጊዜ፡ በሪቫይቫሉ ደስታ ብዛት፡ ያለ እርሱ ርቀው ተጓዙ። ዛሬም በእኛ ላይ እጅግ ተመሳሳይ ነገር እንደሚገጥመን አምናለሁ፡ ይህም፡ በዚህ ግራ በሚያጋባ ወቅት፡ እና ይህን ታላቅ የሪቫይቫል ከተካፈልን በኋላ ይገጥመናል። በዓለም ዙሪያ ሁሉ ተሰራጭቷል። በእያንዳንዱ ሀገር የሪቫይቫል እሳቶች ተቀጣጥለው፡ እየነደዱ ይገኛሉ፥ ታላላቅ የፈውስ አገልግሎቶች፥ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉ ሰዎች፡ በአሥር ሺዎች እጥፍ በሺዎች የሚቈጠሩ ናቸው። በዚህም ስሜት፡ ልክ እንደ እነዚያ ደቀ መዛሙርት እርሱ ያደረገውን ሁሉ

ሲመሰክሩ፡ “ኦህ፡ **ይህን** ሲያደርግ፡ አይተነዋል፡ **ያንን** ሲያደርግ አይተነዋል፡” ብለው እንደመሰከሩ፡ እኛም ያለ እርሱ ሄደናል ብዬ አምናለው።

74 ሪቫይቫሉ ባ—ባመጣቸው ታላላቅ ዕድሎች ተወስደናል። ብዙ ገንዘብ በመሰብሰብ፡ ቤተክርስቲያኖችን በመገንባት፡ ታላላቅ ሕንጻዎችን መንባት፡ ባለ-ሚሊዮኖች-ዶላር ቅንጡ ቦታዎችን፡ ታላላቅ ትምህርት ቤቶችን፡ የትምህርት ሥርዓቶችን፡ እና የሃይማኖት ድርጅቶቻችንን የምናሳድግበት እድሎች አግኝተን ጠፍተናል። የኮሚኒዝም ፕሮግራሞቻችን ማካሄድ፡ ፀረ ኮሚኒዝም፡ ዛሬ የምናወራቸው እነዚህ ብቻ ናቸው። ከሁሉ በፊት ልታውቁት የሚገባ ነገር፡ ሰይጣን በፀረ ኮሚኒዝም ፕሮግራሞቻችን ላይ አይቶናል፡ በታላላቅ የሃይማኖት ፕሮግራሞቻችን ላይ፡ “በባለ ሚሊዮኖች፡” ሌሎች ፕሮግራሞቻችን ላይና፡ በመሳሰሉት ላይ አይቶናል።

75 እሳቱ እስኪቀዘቅዝ ድረስ ከጥንቱ-ዘመን ዓይነት የጸሎት ጉባኤዎች እና ከሚወርደው መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ርቀን ተጉዘን ጠፍተናል። መጮኽም ሆነ፡ ሰዎችንም ወደ መሠዊያው ለማምጣት መሞከር ትችላላችሁ፡ ወደ መድረኩ ሲመጡም፡ በፍርሃት እንደሞተ ሰው ተራምደው ሊመጡ ይችላሉ። ከዚያም አገልጋዮች መጥተው እንዲጸልዩላቸው ትጋብዛላችሁ፡ “ኦህ፡ ለምን ጠየቀኝ? ” እነርሱም ይመጣሉ፡ እነርሱንም ማሳተፍ የማይቻል ነው። ለጥቂት ደቂቃዎችም እዚያ ይቆማሉ፡ ወደ እናንተ ይመለከታሉ፡ ተመልሰውም ወደ መቀመጫዎቻቸው ይሄዳሉ። ለኔ፡ እሳቱ ጠፍቷል! የሆነ ነገር ሆኗል። አዳምጡ! የሚያስፈልገን ሪቫይቫል ነው፡ ኃጢአተኞች፡ ወደ ክርስቶስ በመመልከት፡ ንስሐ እንዲገቡ፡ እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው ወደ መሠዊያው እንዲሮጡ፡ ለምሕረት እንዲጮኹ፡ መላው ቤተክርስቲያንም ከእግዚአብሔር ክብር ጋር፡ የእሳት ነበልባል እንድትሆን ሪቫይቫል ያስፈልገናል።

76 የሃይማኖት ድርጅቶቻችን እንዲያድጉ የሚያደርጋቸውን ዕድል የማግኘት ጉጉታችን፡ አገልጋዮቻችንን ለማስተማር ትላልቅ ትምህርት ቤቶችን ገንብተናል፡ ከመጀመሪያ ከነበሩት በበለጠ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲርቁ እናደርጋቸዋለን። እግዚአብሔር በትምህርት አይታወቅም። በሥነ መለኮትም አይታወቅም። እግዚአብሔር የሚታወቀው በእምነት ነው። እግዚአብሔርን መተንተን አይቻልም። ከትንተና በላይ ነው።

77 ጴንጤቆስጤ የነበርን እኛ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ ሰራችንን ተመልከቱት። ሴቶቻችን ፀጉራቸውን አሳጥረው፡ ሜካፕ አድርገዋል። ሰዎቻችን ተስማምተዋል። አገልጋዮቻችንም ፈቅደዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ መናገር ይፈራሉ። ይህን ከተናገሩ ቤተክርስቲያን ታባርራቸዋለች። ኦህ፡ ከመድረኩ እስከ ምድር ቤቱ ድረስ፡ ቤቱን ማጽዳት ካላስፈለገን። ያሳፍራል። ውርዴት ነው።

78 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ አንድ ሰው ወደ እኔ መጥቶ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ሕዝቡ ይወድሃል፡” አለኝ። ነገር ግን እንዲህ አለ፡ “ሁልጊዜም ትጮህባቸዋለህ፡ ሰለ አጭር ጸጉርና እንደዚህ ሰላሉ ነገሮች፡ በሴቶች ላይ ትጮህባቸዋለህ።”

እንዲህ አልኩት፡ “መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያለ ነገር ማድረጉ ለእሷ ውርደት እንደሆነ ይናገራል።”

79 ይህን ስታደርግ ባሏን ታዋርዳለች። ይህም ከእግዚአብሔር የራቃችሁ ለመሆኑ ፍፁም ምልክት ነው። የሳምሶን ረጅም ጸጉር፡ ከዓለም ተለይቶ ወደ እግዚአብሔር ቃል የገባ ናዝራዊ እንደሆነ፡ ምልክት እንደነበር፡ አስታውስ። ሴቶች፡ ፀጉራችሁን ስታስቆርጡ፡ ናዝራዊ ምልክት እንደሆናችሁ ትክዳላችሁ። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ከመመለስ ይልቅ ወደ ሆሊዉድ ሄዳችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "አይቆረጡ" ይላል። እያችሁ፡ አሳፋሪ ነው፡ አገልጋዮችም ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይናገሩም።

80 ይህ ሰው እንዲህ አለኝ፡ "ለምን ሴቶቹን አትተዋቸውም? " አለኝ፡ "አንተን ነቢይ አድርገው ይቆጥሩሃል" አለኝ።

እኔም፡ "እኔ ነብይ ነኝ ብዬ አላውቅም።"

81 እንዲህ አለኝ፡ ''እንደዚያ አድርገው ይቆጥሩሃል። መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንዴት መቀበል እንደሚችሉና አንድ ነገር እንዲያደርጉ አስተምራቸው። ትልልቅ ነገሮችን፡ ታላላቅ ነገሮችን ልታስተምሯቸው ይገባል።"

82 እኔም፡ "በጨዋነት መኖር እንዴት እንደሚችሉ ሃሁ ሳይማሩ፡ አልጀብራን እንዴት ማስተማር እችላለሁ? ይህ እንዴት ማድረግ ይቻላል? አዎን፡ ወደ መጀመሪያው ነገር በመመለስ።"

83 ከዓመት ወደ ዓመት፡ አገሪቱን እያቋረጠ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ይሄዳል። የሆነ ቦታ የሆነ ችግር አለ፡ ከቃሉ አይደለም። የሪቫይቫል እሳቶችን ማቀጣጠል አለመቻላችን ምንም አያስደንቅም። የቤት ፅዳት ጊዜ ያስፈልገናልና። እስካልተመለስን ድረስ እግዚአብሔር ያንን አያደርግም። የቤት ፅዳት ጊዜ ያስፈልገናል።

84 አንተ ሰው፡ ሚስትህ እንዲህ ያለ ነገር እንድታደርግ፡ አጫጭር እንድትለብስ ታደርጋለህ! ሜቶዲስት፡ ባፕቲስትም እንኳ አይደሉም። ጴንጤቆስጤዎች ናቸው፡ በትክክል፡ "የአምልኮት መልክ፡ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ለብ ያለ፡" ጴንጤቆስጤነትን በስም ብቻ፡ በቃ። ጴንጤቆስጤ ስም አይደለም፡ ሰዎችን የሚያነጻ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ ነው። ታላቅ ፈውስ አገልግሎቶችና ሌሎች ነገሮችን ማግኘት አለመቻላችን ምንም አያስገርምም፡ የሆነ ቦታ የሆነ ችግር ተፈጥሯልና። እኛን ያየን፡ ይህ ሰይጣን ነው...

85 "እንግዲህ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳች ነገር ብንናገራቸው፡ አባልነታቸውን ይለውጣሉ።"

86 አስታውሱ፡ ክርስቲያኖችን ማባበል አይገባም። ክርስቲያኖች ብርቱዎች ናቸው። ሌላ ሰው ምንም ይበል አይበል፡ ስለ እግዚአብሔር የሚጸኑ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ናቸው። እነሱን መለመንና ማሳመን፡ ሽቶ መቀባትና እንደ ህጻን እሹሩሩ ማለት አይጠበቅባችሁም። ያ'ማ የሞቀ አልጋ፡ የተዳቀሉ ተክሎች፡ በጭራሽ አይጠቅሙም፡ በጭራሽ አያፈሩም።

87 በ... በቅርቡ ማረፊያ ጊዜ እንደሚሆን፡ ያስታውሰኛል። ዛሬ እዚያ፡ ትናንሽ ወፎችን አስተውዬ ነበር፡ ትናንሽ ድንቢጦች ገለባን ወደ ጎጆዎቻቸው ሲያስገቡ አየሁ። ትናንሽ እንቁላሎቻቸውን እንዲፈለፈሉ፡ ጎጆ እስኪሰሩ ድረስ ረጅም ጊዜ አይቆይም። ታውቃላችሁ፡ አንዲት ወፍ እንቁላል የያዘ ጐጆ ሲኖራት፡ በእንቁላል ጎጆው ላይ ቁጭ ትልባቸዋለች፡ በየጥቂት ደቂቃዎቹ ታዞራቸዋለች፥ ትናንሽ

እግሮቿን ተጠቅማ ታዞራቸዋለች፡ እዚያም ትቀመጥባቸዋለች። አሁን፡ ከሞቁ በኋላ፡ እንቁላሎቹ እንዲቀዘቅዙ ካደረገች፡ አይፈለፈሉም። በርራ ትሄድና አፏን በምግብ ሞልታ ትመለሳለች፡ እንደገናም ትቀመጥባቸዋለች።

88 ታውቃላችሁ፡ ይህች እናት ወፍ፡ በእንቁላሎቹ ላይ ትቀመጥባቸዋለች፡ በየ ሁለት ደቂቃም ትገለብጣቸዋለች፡ እና ፈጽማ... በጾም እና በመሰዋዕትነት ድሃ እስክትሆን ድረስ ከጎጆዋ አትወጣም። ይሁን እንጂ፡ እናት ወፍ፡ ከወንዱ ወፍ ጋር ካልተገናኘች በስተቀር፡ እንቁላሎቹ አይፈለፈሉም። ምንም ይሁን ምን፡ ምንም ያህል ቢንከባከቧቸውም፡ አይፈለፈሉም። በጎጆው ላይ እንደታቀፉ ይበሰብሳሉ።

89 ጴንጤቆስጤም ከወንዱ ባሏ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የምትገናንበት ጊዜው ከተባለ ይህ ነው፥ ምክንያቱም ጎጆው እምነትን በካዱ፡ ወደ ኢኪሜኒካል ካውንስል በተቀላቀሉ፡ በበሰበሱ እንቁላሎች ተሞልቷል፡ ከጳጳሱ አጠገብ መቀመጥ፡ “መንፈሳዊነት ነው” ይሉታል፡ ታላቅ ነገር ነው ይላሉ። እናንተ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ የዓለማችን ችግር ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያሉ ነገሮች እንደሚፈፀሙ አስቀድሞ እንደተናገረ አታውቁም ወይ? ሜቶዲስቶች እና ባፕቲስቶች ሌሎች እንደዚህ ያሉ ነገሮች ወደ እኛ ስለመጡ፡ ዕልል ትላላችሁ። ሰነፏ ድንግል ዘይት ለመግዛት ስትወጣ፡ ሙሽራው የመጣው በዚያው ሰዓት መሆኑን አታውቁምን? ዘይቱን አላገኙም! ይኸውላችሁ፡ ንጥቀጥ በምስጢራዊ አመጣጥ ይመጣል፡ ከዚያም በእነዚያ ቀናት፡ ይሄዳሉ፡ እናንተ ግን መፈጸሙን እንኳ አታውቁትም። ጥሏችሁ ይሄዳል፡ ከዚያም ምን እንደሆነ ራሳችሁን ትጠይቃላችሁ።

90 ልክ ዮሐንስ ወደ ምድር እንደ መጣ ይሆናል። እነርሱ እንዲህ አሉት፡ “መልካም፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት አለበት ይላል፡” አሉት። እርሱም “ከዚህ በፊት መጥቷል፡ እናንተ ግን አላወቃችሁትም፡” አላቸው።

91 አንድ ቀን፡ እንዲሁ ይሆናል፡ ያን ጊዜ እንዲህ ይላሉ፡ “ይህ የሚሆነው ከመከራው ዘመን በፊት ነው ብዬ አስቤ ነበር። መነጠቅ ሊሆን ነው ብዬ አስበ ነበር ይላሉ።” ቃላቱ ወደ ኋላ ሊመለሱ ይችላሉ፡ “ከዚህ በፊት ተፈጽሟል አላወቃችሁትም።” አይ-ሃህ። ካሰባችሁት በላይ አርፍዳችሁ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ ንቂ! ባቆመው የተሻለ ነው፥ እዚህ በጭራሽ ለዶክትሪን አልመጣሁም፡ ጎን ለጎን ይህንንም እንድትረዱ ብቻ ብዬ ነው የተናገርኩት።

92 አስታውስ፡ ወንድሜ፡ ሰይጣን እነዚህን ትላልቅ ፕሮግራሞችን ተመልክቷል፡ አንዲት ቤተክርስቲያን ሌላዋን ለማሸነፍ ትሞክራለች፡ አንድ የሃይማኖት ተቋም ሌላውን ለማሸነፍ ይሞክራል፡ ሁሉንም ማንበብና መጻፍ አለመቻልን ካለፉ በኋላ የሥነ ልቦና ፈተና እንዲሰጣቸው ማድረግ፡ አንድ ሰው ወደ ተልዕኮ መስኮች ከመሄዱ በፊት የሥነ ልቦና ባለሙያ እንዲፈትነው ማድረግ። ጴንጤቆስጤ ሆይ! አይደለም፡ እ—እ—እንዲህ የሚያደርገው ፕሬስባይተሪያን አይደለም፡የጴንጤቆስጤ ነው። አንድ የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮች ቡድን አለ፡ ትልቅ ቡድን፡ ወደ ሚሽን ስራ መስክ ከመውጣታቸው በፊት፡ የስነ ልቦና ምርመራ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።

93 ምርመራቸው እንደዚያ ቢሆንስ ኖሮ? እነዚያም ተመርመረው ነበርና። በመጀመሪያ የጴንጤቆስጤ ምርመራ ተደርጎ ነበርና፡ ከሰማይ እሳት እና የእግዚአብሔር ኃይል እስኪወርድላቸው ድረስ፡ በላይኛው ሰገነት ላይ ጠበቁ። ምርመራቸውም ያ ነበር።

94 መጠጥ-ቀማምሶ የመጣ ዓለማዊ ሳይኮሎጂስት፡ አይምሯቸውን አልመረመራቸውም፡ ትንሽ ስሜታዊ ከሆንክ፡ ወይም ሌላ ነገር ካለ፡ “አንተ ገና ነህ አልተዘጋጀህም፡” ይሉሃል። ግን'ኮ ሰው፡ እጅግ መንፈሳዊ ሲሆን ጭንቀታም እንደሚሆን የታወቀ ነው፡ ወደ መንፈሳዊነት ለመግባት በዚያ ሁኔታ ውስጥ መሆኑ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ይኸውላችሁ፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔር ለዓመታት ለማድረግ የሞከረውን ነገር እያበላሻችሁ ነው፡ በታላላቅ ፕሮግራሞቻቸው ላይ ተመልሳችችሁ...

95 ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ሲያዩ በጣም ይደሰታሉ። እንዲህ ይላሉ፡ “እነዚህን ሁሉ አሴምብሊ ማድረግ በቻልኩ! እነዚህንም ሁሉ ዋንነስ ማድረግ በቻልኩ! እነዚህንም ሁሉ ሜቶዲስት ማድረግ በቻልኩ!” ሜቶዲስቶች ሌሎችን ሁሉ ሜቶዲስት ለማድረግ ይፈልጋሉ፡ ባፕቲስቶች ሌሎችን ሁሉ ባፕቲስት ለማድረግ፡ ጴንጤቆስጤዎች ሌሎችን ሁሉ ጴንጤቆስጤ ለማድረግ ይሞክራሉ! ኡህ፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ወሰኗቸዋልና፡ አንዳች መቀየር አትችሉም። ወንጌልን ብቻ እንሰበክ። በቃ። ታላላቅ ፕሮግራሞቻችን፡ ግን፡ ያለምንም እሳት ቀርተዋል። ጠፍተናል፡ ቀድሞ እንደነበረው እሳታችንን የቤት ውስጥ እሳት አድርገነዋል።

96 እና ኮሚኒዝማችን፡ አሁን በጣም ፈርተናል፡ ኮሚኒዝም ገብቷልና፡ “ምን ሊሆን ነው? ” ታውቃላችሁ ግን፡ ታላቁ ነገር፡ ኮሚኒዝም አይደለም። አሁን ይህን እንድነግራችሁ ፍቀድሉኝ፡ እኔ ኮሚኒዝምን አልፈራም።

97 እኔ የምፈራው፡ እናንተ የጴንጤቆስጤ ሰዎችን ነው፡ ይህ ዓለም አቀፋ የቤተክርስቲያናት ካውንስል ይወስዳችኋል። ጉዳዩ ያ ነው። ይህም የአውሬውን ምልክት የሚሰራ ይሆናል፡ እናንተም እርሱን ለመቀበል ትቀላቀላላችሁ። ምክንያቱም ድርጅት ናችሁ፡ መግባት ወይም መውጣት ይኖርባችኋል። ጉዳዩ ያ ነው፡ ማንኛውም ብልህ፡ አስተዋይ፡ መንፈሳዊ ሰው ይህን ያውቃል። ሌላ የባሕር-ላይ-ምስክርነት ያስፈልገናል፡ አሁንም አግኝተነዋል። የእኛ የጴንጤቆስጤዎችም፡ ያገኙትን ሁሉ ይውጣሉ፡ መንጠቆውንም፡ ገመዱንም እና ሜንጦውንም ይውጣሉ፡ “እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ይሆናል!” የሜቶዲስት፡ የፕሬስባይተሪያን፡ የሉተራን፡ የክርስቶስ ቤተክርስቲያንና የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮች፡ ወደዚያ ለመቀላቀል፡ ታላቁን የሐዋርያዊ አስተምህሮ ትክዳላችሁ። ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ጋር ምንም አንድነት አይኑራችሁ። አሰቀድሞ እንደተረጋገጠው፡ ከሮም ጋር ሕብረት እየፈጠሩ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ይላሉና።

98 ሰባኪዎች ሕዝቡን ሳያስጠነቅቁ እነዚህ ነገሮች በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ፡ የፈቀዱት ምንድነው ችግራቸው? እግዚአብሔር ከእጃቸው ይፈልገዋል። በዚህ ችግር ጊዜ ውስጥ፡ በችግር ውስጥ ነበሩ፡ እንደዛ ነበሩ። የኮሚኒዝም ሥርዓት አይገባባትም፥ መንጋውን በሙሉ የሚውጠው የዓለም አቀፉ አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ነው። እንዲህ ስትናገሩ፡ አስታውሱ፡

“አይሆንም... ” ስትሉ ይሆናል፡ ከዚያ በጣም ይረፍድባችኋል። የአውሬውን ምልክት ይወስዳችኋል። ስለዚህ የአውሬው አባል ናችሁ።

99 አሁን ከዚህ ለማምለጥ ወደምትችሉበት ቦታ ብትሄዱ ይሻላል፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ታተሙ። የክርስቶስ አካል በመንፈስ ቅዱስ ወደ እርሱ የተጠመቅንበት፡ የክርስቶስ ምስጢራዊ አካል ነው፥ የምንቀላቀለው፡ ወደዚያም የምንወስድ፡ እንድንገባ የሚነገረን፡ ወደዚያም ለመግባት-በልሳን-የምንናገርበት፡ የምንጮኽበት አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ፡ በውስጡ ተወለዳችሁ። በትክክል። በእርግጠኝነት።

100 እና ይህን አስተውለናል፡ ችግሩ በድንገት መጣባቸው። ኦህ፡ ዲያቢሎስ ተመለከተና እንዲህ አለ፡ “አሃ-ሃህ፡ እነሆ በታላቅ ጉስማዎች ወጥተዋል፡ ወደላይ-እና-ወደታች እየዘለሉ፡ እየጮሁ፡ ትልቅ ጊዜ እያሳለፉ ነው። ይኸውላችሁ፡ እነሱን የማስጥምበት ጊዜዬ አሁን ነው። አሁን’ኳ እብሬአቸው መሆንም እችላለሁ።”

101 ስለዚህ ወደ ኮረብታው ወጥቶ መርዛማ ትንፋሹን መተንፈስ ጀመረ፡ ፒውፍፍ፦ “የተአምራት ቀናት አልፈዋል። ቀድሞውኑም፡ እነዚህ ሰዎች ጭንቀት እንዳለባቸው አምናለሁ። ወደ መስክ ከመውጣታቸው በፊት የ—የ—አዕምሮ ምርመራ ማድረግ አለባቸው ብዬ እሰባለሁ።” ጴንጤቆስጤዎች ሆይ! አሃ-ሃህ። ቃሉን የሚገድል መርዛማ ትንፋሹን ተመልከቱይ፡ “ኦህ፡ ሌላ ነገር ይመስለኛል፡ እኔ እ—እምናለሁ... ” እያችሁ፡ ሌሎቹ የሃይማኖት ተቋማቶች እንዳደረጉት ወዲያው ወደ ኋላ ይመለሳሉ፡ የሚጓዙበት መንገድ በዚያው ነው። ሁሉም፡ ያም፡ ይገድለዋል። በተደራጀህ ቅጽበት፡ ይገድለዋል። ሁሌም እንዲሁ ነው። ሁሌም ይቀጥላል። ዳግመኛ አይነሣም። በታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ነው። በዚህ—በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ክርስቶስ ከቤተክርስቲያኑ ውጭ ሆኖ፡ እያንኳኳ፡ ወደ ውስጥ ለመግባት እየሞከረ ነበር። ሊቀበሉትም አይችሉም። ሊያዳምጡት አይችሉም። አሁን በምንኖርበት ዘመን፡ ችግር እንደተፈጠረ፡ እናውቃለን።

102 ከዚያ በኋላ፡ ቀድሞ የነበሩት ተአምራቶች፡ እንደቀሩ ማስተዋል እንጀምራለን። ህመምተኞች ከህመማቸው ጋር ይመለሣሉ። የዚህ ምክንያት እግዚአብሔር አይደለም። በሕዝቡ መካከል ሪቫይቫል ባለመኖሩ ነው። ሪቫይቫል የለም። ቁጭ ብለው ያ—ያዳምጣሉ፥ ወደ ቤታቸው ይሄዱና፡ እንዲህ ይላሉ፡ “መልካም፡ በጣም ጥሩ ነበር ብዬ እገምታለሁ። አሃ-ሃህ።” እያችሁ፡ ያ መቅናት የለም። በህዝቡ ውስጥ መሆን ያለበት ነገር የለም።

103 ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት፡ እዚህ አርካንሳስ ውስጥ፡ በጆንስቦሮ ትንሽ ስብሰባ አድርጌ እንደነበር አስታውሳለሁ፡ ወደ አርባ ሺህ የሚጠጉ ሰዎች በስብሰባ ላይ ለመገኘት ሲሞክሩ፡ አሥራ አምስት ሺህ የሚጠጉ ሰዎች በሚኖሩበት ከተማ ወደ ስብሰባው መጡ። ወደ ውስጥ ለመግባትም፡ በታመሙ ልጆቻቸው ላይ ችግራቸውን በወረቀት እየጻፉ፡ በጥጥ የጭነት መኪናዎች እና በሌሎች ነገሮች ሥር ተኝተው ነበር። በወንበራቸው ላይ ተቀምጠው ቀንም ሆነ ማታ፡ ቦታቸውን አይለቁም ነበር፡ ቤተሰቦቻቸው ሀምበርገርና የ—ፖፕ መጠጥ እንዲያመጡ ይልኳቸው ነበር፥ እዚያው ይቆያሉ፡ ከቀን ወደ ቀን፡ ከቀን ወደ

ቀን፡ ልባቸው፡ በእሳት እየነደደ ነበር። እግዚአብሔር ያደረገላቸው ትንሿ ነገር፡ በእሳቱ አቀጣጠላቸው። በመቶዎች የሚቈጠሩ ሰዎች መጡ።

104 ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት የነበረው እግዚአብሄር፡ ዛሬም ቢሆን፡ ያው ነው። ዛሬም ቢሆን፡ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ጊዜ እንደ ነበረው እግዚአብሔር፡ አሁንም ያው ነው።

105 ታዲያ ምንድነው? ሁላችንም በመጓጓት ድርጅቶቻችንን መገንባት ፈልግን፡ **ይህን** መገንባት፡ **ይህንን** መገንባት ፈለግን፡ ታላቅ እና የሚያብረቀርቅ ነገር ፍለጋ፡ ከነ ጆንስ ጋር፡ ከሜቶዲስት ጋር፡ ከባፕቲስት ጋር፡ ከፕሬስባይተሪያን ጋር ማወዳደር ፈለግን። እናንተ የእነርሱ ወገን አይደላችሁም። በጭራሽ፡ አይደላችሁም። እነሱ የሃይማኖት ተቋም ሰዎች ናቸው፡ እሱም ይሁን፡ እነርሱን መቃወሜ አይደለም። በመካከላቸውም ብዙ ጥሩ ክርስቲያኖች አሉ፡ እናንተ ግን ከእነዚህ ከማያምኑ ጋር መቀላቀል የለባችሁም። “ኃይሉን ከካዱ ሰዎች፡” ከእነርሱ ጋር አትወግኑ።

106 ይኸውላችሁ፡ ችግሩ፡ ሆሊዉድን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማስገባት መሞከራችሁ ነው። ማድረግ ያለባችሁ ሆሊውድን ከቤተ ክርስቲያን ማስወጣት ነው። እያችሁ? ህንጻዎቻችሁ እጅግ ውብ ለማድረግ ትጥራላችሁ፡ የሐይማኖት ተቋማችሁን ለማስተለቅ ጥጥራላችሁ፡ ይህም የሰዎችን ትኩረት እንዲስብላችሁ ነው። እነርሱን ወደኛ ማምጣት አለብን እንጂ። እኛ ወደነሱ እንሂድ። ሁሉም ነገር የሚያንጸባርቅ ነው፡ አስታውሱ፡ ሆሊዉድ መብለጭለጭ ከአለማዊነት ጋር ነው፡ ወንጌል ግን በትሕትና ያበራል። በሚያንጸባርቁና በሚያበሩ ነገሮች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ወንጌል በትሕትና፡ በየዋህነት፡ ዝቅ በማለትና፡ በኃይል ያበራል። ሆሊውድ፡ ሲያንጸባርቅ፡ ሁሉም እየተንጫጩና እየጮሁ፡ ወደ እሱ ይሄዳሉ። እያችሁ? ያ አያስፈልገንም።

107 እንዲህ ዓይነቱን ብርሃን መኖር እንፈልጋለን። “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፡” ብሏልና። “ጨው ጣዕሙን ቢያጣ ግን፡” ማለት በወንጌል ውስጥ ያለው ጥንካሬ ነው። በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የሚንቀሳቀስ ነገር ሊኖረን ይገባል ያን ጊዜ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያኖች፡ ሌሎችም ለመምጣት ይናፍቃሉ። ጨዋማ መሆን አለብን! ጨው ጥማትን ያመጣልና፡ ጥም ይፈጥራል። ጨው የነካው ነገር ሁሉ፡ ይጣፍጣል። መነካካት ግን አለበት።

108 ቁጣዎቻችን ከሜቶዲስት እና ባፕቲስት ጋር ለማነጻጸር እንደምንሞክር፡ ይታወቃል፡ በትላልቅ ሕንጻዎችና በትላልቅ ቦታዎች፡ በጥሩ በተማሩ ሰዎች፡ በትላልቅም ትምህርት ቤቶችና በትላልቅ ኮሌጆች፡ እንደዚህ ባሉ ነገሮች ሁሉ ማነጻጸር ይፈልጋል። በቁጣ ጠፍተናል፡ እነሆ ችግር ደረሰብን።

109 መንፈሳዊ አእምሮው ያለውም አይቶ እንዲህ ይላል፡ “እዚህ ጋር፡ ቆይ አንዴ፡ ሁላችንም ያንን ኢኩሜኒካል ካውንስል እንቀበላለን ማለት ነው? ወገኖቻችን በሙሉ ይቀላቀሉታል ማለት ነው? ” አዎን፡ ሁላችሁም ትሄዳላችሁ። በትክክል። እንዲህ ካልሆነ ጠብቁና እዩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ እንደሚሆን ተናግሯል፡ በትክክል፡ ክርስቶስም ከውጭ ይሆናል። ከሊቀ ጳጳሱ በፊት ጨረቃ ጨለመች (የመጀመሪያው ወደ ሮም በሄደ ግዜ)፡ ባለፈው ምሽት፡ በሰማያት

ላይ ምልክት እያሳያችሁ ነበር። በልተጠበቀ መንገድ፡ አደረገው። በዛሬው ጊዜ ጌታ እንዴት አስደናቂ ነገሮችን፡ እያደርገ ነው!

110 ከዚያም በዚህ ታላቅ ጨለማ ሰዓት፡ እዚያ በነበሩ ጊዜ፡ ንፋስ ተነሣ። በሕይወት የመትረፍ ተስፋ ሁሉ ጠፋ። አሁን ደግሞ የሃይማኖት ተቋማችሁ ወደ ዓለም አቀፉ አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ከተቀላቀለ ምን ታደርጋላችሁ? በዚህች ምድር ላይ የገነባናቸው ታላላቅ ነገሮች በሙሉ የመጨረሻው ተስፋቸው ከጠፋ በኋላ፡ ምን ይሆናል?

111 ነገር ግን ይኸውላችሁ፡ ተስፋ ሁሉ ጠፍቶ፡ መዳን አቅቷቸው፡ ሊጮኹ ሲሉ፡ በድንገት፡ በውኃው ላይ እየተራመደ ሲመጣ፡ አዩት። በጨለመ ጊዜ፡ የተራመደ፡ መጣ።

112 ይኸውላችሁ? ገና ትቷቸው ሲሄድ፡ ይህ እንደሚሆን ያውቅ ነበር፡ ስለዚህ በአገሪቱ ውስጥ ወደሚገኘው ከፍተኛው ኮረብታ ወጣ። ከፍ ባላችሁ ቁጥር፡ እሩቅ ታያላችሁ። እነሱን መመልከት ይችል ዘንድ ወደ ላይ ወጣ፡ ታውቃላችሁ።

113 ይህ እንደሚመጣ ያውቅ ነበር። ይህ ቀን እንደሚመጣ ተንብዮ ነበር። “በሰዶም ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል። የሰው ልጅ ሲገለጥ።” ማለት፡ ልጁ ይገለጣል። ይህ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል። ምልክትም ይሰጠዋል። በዚያን ጊዜ እንዳደረጉት ይቃወሙታል፡ ነገር ግን የትንሣኤው ምልክት ይሆናል። ድሮ ያረገውን እያደረገ፡ አሁንም ህያው ነው።

114 በዚህ ታላቅ ሰዓት፡ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በጭንቀት ውስጥ ሳሉ፡ ያያቸው ዘንድ ወደ ላይ እንደወጣ፡ እናያለን። በከፍታው ላይ ተቀምጦ፡ ይመለከታቸዋል።

115 በዚህ ጊዜ ተራራ ላይ አልወጣም፡ ነገር ግን ከመቃብር ወጣ፡ በደመናትም አረገ፡ ከጨረቃ፡ ከከዋክብት ባሻገር፡ ሰማያትን ወደ ታች እስከምያይ ድረስ በጣም ከፍ ብሎ ወጣ። በዚያም፡ በከፍታ ላይ ተቀመጠ። አሁን አይኖቹ በድንቢጦቹ ላይ ናቸው፡ እየተመለከተን መሆኑን አውቃለሁ። እያየን ነው።

116 በዚህም በጨለማ ዘመን፡ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ወደ ታላላቅ ፕሮግራሞች ሲገቡ፡ **ይህንን** ፕሮግራምና **ያንን** ፕሮግራም አላቸው፡ ሁሉም እንደሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የተደራጁ፡ የሃይማኖት ተቋም ናቸው። ምን ተፈጠረ? በጨለማው ዘመን፡ በመንፈስ-የተሞሉ እውነተኛ ሰዎች እንዲህ ብለው ሲጠይቁ፡ “ምን ሊሆን ይሆን ሲሉ? ልጆቼን ተመልከቱ!” ሰውየው፡ “ሚስቴን ተመልከቱ! **ይሄን** ተመልከቱ!”

117 እሁድ፡ ወይም ረቡዕ ማታ ከጸሎት ሰብሰባ፡ ቶሎ በመውጣት፡ **ዊ ላቭ ሉሲን፡** ወይም እንደዚህ ያለ ነገር፡ በቴሌቪዥኑ ላይ ለማየት ይቸኩላሉ። “ከእግዚአብሔር ይልቅ፡ ዓለምን የሚወዱ።” እንደነዚያ ናቸው።

118 በቀደም እንዲት እመቤት ሰውነቷን አጥብቆ የምይዝ ልብስ ለብሳ ነበርና፡ ተናገርኳት። እንዲህ አልኳት፡ “እህቴ፡ አለባበስሽ በጣም ጠባብ ነው። መናገሬ ጥሩ ላይመችሽ ይችላል፡ ግን እንደዛ ነው። ክርስቲያን እንደመሆንሽ መጠን፡ ለሰዎች ዕንቅፋት ትሆኛለሽ።”

119 እሷም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ታውቃለህ? ” “የሚያመርቱት ይህን ዓይነት ብቻ ነው፡” አለችኝ።

120 እኔም፡ “ይህ ምክንያት አይሆንም። አሁንም መሳሪያዎች ይሸጣሉ፡ የልብስ ስፌት ማሽኖች አሏቸው።” አዎን።

121 ስማኝ፡ አንድ ነገር ልንገርህ፡ ውድ ወዳጄ ሆይ። እየኮነንኩህ አይደለም። አይደለም፡ ወዳጄ። ከሰቃይ ውስጥ ላወጣችሁ እየሞከርኩ ነው። ይህ መንፈስ በውስጣችሁ እስካለ ድረስ፡ ታመልጣላችሁ። በትክክል። ከዚያ መወለድ አለባችሁ። አሁን እንደፈለጋችሁ መናገር ትችላላችሁ፡ አንድ ነገር ግን ልንገራችሁ፡ እያችሁ፡ “ንብረታችሁ ባለበት፡ በዚያ ልባችሁ ይሆናል።”

122 አንድ ነገር ልነግርሽ። ለባልሽ እንደ ጽጌሬዳ አበባ ንጹህ ልትሆኚ ትችያለሽ፡ ለወንድ ጓደኛሽም፡ እንደ ጽጌሬዳ አበባ፡ ንጽሕት ወጣት ልጃገረድ ልትሆኚ ትችያለሽ፡ ነገር ግን አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ስለ ምንዝርናሽ መልስ ትሰጪበታለሽ። እንደዛ ስትለብሺ ጥፋተኛ ነሽ። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም፡ ያን ጊዜ በልቡ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሯል።” ሃጥያተኛውም፡ አንቺን በማየቱ፡ ምንዝርና በመፈጸሙ መልስ ሲሰጥ፡ ወደዚያ የዳረገው ማን ነው? አሰቢበት። እናንተ የጴንጤ ሴቶች ሆይ፡ አፈርንባችሁ! እያችሁ? ታሳፍራላችሁ!

123 እንዲህ እንድናገራችሁ የሚያደርገኝ፡ ስለምወዳችሁ ነው። ፍቅር ይገስጻልና።

124 በታላቅ ውጥንቅጥ ገብተናል፡ አለባበሳችን ውጥንቅጥ ነው። ልክ፡ እንደ ዓለም ፋሽን ነው። እርሱም “ዓለምም ሆነ፡ በዓለም ያሉትን ነገሮች አትውደዱ፡ ዓለምን ከወደዳችሁ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችሁ የለም፡” ብሎናል። ምንም ያህል በልሳን ብትናገሩ፡ ወደ ላይ እና ወደ ታች ብትዘሉ፡ ብትጨፍሩ፡ ጸጉራችሁን ብትቆረጡ፡ እንደዚህ ዓይነት ልብሶችን ብትለብሱ ምንም ግድ አይሰጠኝም። አንተ ይህን የምትፈቅድ ሰው። የገዛ ፍሬህ የት እንዳለህ ያሳያል። ይህ በትክክል እውነት ነው። አሁን በገባንበት አዘቅት መግባታችን፡ የኮሙኒዝም ንፋሳት መብዛታቸው፡ የቸርቻዊነት ንፋሳት መብዛታቸው፡ የኢኩሜኒካልል ድርጅቶች ንፋሳት መብዛታቸው አያስገርምም!

125 ይህ የ—የመቀላቀል ጊዜ ነው፡ አንድ የመሆን ጊዜ ነው። ማህበራት ሰራተኞችን እያደራጁ ይገኛሉ፡ በዚያም ይመካሉ። መንግስታት፡ የ—የተባበሩት የመንግሥታት ድርጅት አላቸው፡ አንድ እየሆኑ ነው። አብያተ ክርስቲያናትም እየተደራጁ ነው። ይህ ሁሉ ምን ያሳያል? ይህ የሚያሳየው ክርስቶስና ሙሽሪት አንድ ለመሆን እየተዘጋጁ መሆናቸውን ነው። የሚናገረው ያንን ነው። እነዚህ ሁሉ የነገሮች ጥላዎች የሚመጣውን አዎንታዊ ነገር እያሳዩ ነው። አሁን ልንጨርስ ስለሆነ ተመልከቱ፡ በጣም እየዘገየሁ ነውና።

126 አሁንም አስተውሉ፡ በሕይወት የመትረፍ ተስፋ ሁሉ በጠፋበት፡ በዚያ ታላቅ ሰዓት፡ አንድ ሰው፡ በውኃ ላይ እየተራመደ ሲመጣ አዩ፡ እየተራመደ። እዚህ ጋር፡ በደምብ አዳምጡ፡ የሚያሳዝነው ነገር፡ ሊረዳቸው የመጣውን ብቸኛው ረዳታቸውን፡ ፈሩት። “ምትሐት ይመስላል። ይኸውላችሁ፡ ምትሐት፡ ሊሆን ይችላል፡” ተባባሉ።

127 ይህ ነገር እንደገና አልተደገመም ወይ! ፈሩት። ኢየሱስ ራሱ በዚህ ዘመን ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ተናግሮ ሳለ፡ ጥንቆላ ሊሆን ይችላል፡ የሰይጣን ኃይል ሊሆን ይችላል ብለው ፈሩ። ሊረዳቸው የሚችለው ብቸኛው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌላ የሃይማኖት ተቋም አይደለም፡ ሁሉም ተደምረውም አይረዷችሁም፡ እንደውም ከፊት ይልቅ ከባድ ይሆናል። ሊረዳችሁ የሚችለው ብቸኛው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

128 በመጨረሻውም ዘመን፡ በዚህ መልክ፡ እንደሚመለስ ቃል ሲገባ፡ ቃል ሲገባም (የተሰፋው ቃል ልጅ፡ ማለት የመጀመሪያው ዘር ወደ አብርሃም ከመምጣቱ በፊት እንደሆነ፡) እርሱም የአብርሃም ንጉሳዊ ዘር፡ ኢየሱስ እንዳለ... ተመሳሳይ ነገር እንደሚታይ ተናግሮ ነበር። ቃል የተገባለት ልጅ ከመምጣቱ በፊት፡ እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ ልክ ኢየሱስ እንዳደረገው ያደርጋል፡ አደርጋለሁ ብሎ እንደተናገረ፡ በመቸረሻው ዘመን ይሆናል ብሎ እንደተናገረ አደረገ። ከተገቡ ተሰፋዎች መካከል፡ መዘርዘር የምንችላቸው፡ በደርዘን የሚቆጠሩ እነዚህ ናቸው፡ ሊሆኑ ካላቸው ጥቂቶች፡ እነሆ በአይናችሁ ፊት ነው።

129 እጃቸውን ዘርግተው፡ ሊቀበሉት የሚገባቸው፡ አብያተ ክርስቲያናትም፡- “ያንን ትንሽ ፈርቼዋለሁ። አያችሁ፡ የእኛ ወገን አይደለም።” እጅግ ይንቀጠቀጣሉ። ወደ ክርስቶስ ሊያመጣቸው የሚችለው ብቸኛው ክርስቶስ ራሱ ሆኖ ሳለ፡ እንደ አስፈራሪቾ ይፈሩታል። “ኡህ፡ እንጃ። ይኸውላችሁ፡ ምትሐት ሊሆን ይችላል። በዚህ ነገር ላይ እውቀት የለኝም።” ሊረዳቸው የሚችለው ብቸኛውን ነገር ይፈሩታል።

130 በዚያ ጨለማና ጭንቅ ሰዓት፡ የተመረጡ የተባሉ ቸርቾች፡ በዚያ የተቀመጡ ወገኖች፡ ምትሐት እንዳይሆን የፈሩ፡ ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖራቸው አልፈለጉም። ከዚያም “አትፍሩ፡ እኔ ነኝ።” የሚል ጣፋጭ ድምፅ መጣ።

131 እርሱ ቃል ነው፡ አይደለም’ዴ? ቃል ከመሆኑ፡ ፈጽሞ አይለወጥም። ዛሬ ማታስ ቃሉ እንዲህ ሲላችሁ፡ እርሱም፡- “ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነው። አትፍሩ፡ እኔ ነኝ” ሲል አይሰማችሁምን?

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

132 የሰማይ አባት ሆይ፡ ም——ምሽቱ ይሞቃል። እሳቱ ከመሠዊያው ጠፍቷል፡ ጊዜውም ጨልሟል። አንተም በመስክ ላይ እየቃረምህ ነው። እንዳልከው፡ “መንግሥተ ሰማይ መረብ ይዞ ወደ ባሕር የሄደ ሰው ትመስላለች፡ ወደ ባሕር ጣለውና፡ መልሶ ባወጣው ጊዜ፡ ከሁሉም አይነት የሰበሰበ ይመስላል። መንግሥቱ እንደዚያ ናት።” ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ አንድ ቀን በዚያ ውኃ ውስጥ ያለውን የመጨረሻው ዓሣ! “ከሁሉም አይነት ሰበሰቡ።” ብለሃልና። ይህ የወንጌል መረብ ሁሉንም ዓይነት ዓሣ ይይዛል፡ ኤሊዎችን፡ ፌንጣዎችን፡ ሸረሪቶችን፡ እባቦችን፡ ተናካሹ አሳ። ምን እንደሚይዝ እኛ አናውቅም፡ ይሁን እንጂ አንተ የያዝካቸው ጥቂት አሳዎች ነበሩ። አንተ ብቻህን ዳኛ ነህ። ይሁን እንጂ ኤሊው፡ ፌንጣው ሁሉ፡ እንደገና ወደ ጭቃው ጉድጓድ፡ ወደ ውኃው፡ መመለሳቸውን፡ አውቀናል። አንድ ቀን ግን ኋለኛው እንዲሆን የተመደበው፡

አስቀድሞ የተወሰነው፡ የአካሉ የመጨረሻው ብልት የሆነው አሳ፡ እነሆ ከኃይቁ ይወጣል።

133 በሉተር፡ በዌስሊ፡ በአሌክሳንደር ካምቤል፡ በጆን ስሚዝ፡ በካልቪን፡ በኖክስ፡ በፊኒ፡ በሳንኪና፡ በመሳሰሉት፣ በጴንጤቆስጤ ዘመን፡ በኤፍ. ኤፍ. ቦስዎርዝና፡ በፍሮክማን፡ በእነዚያ ታላላቅ ሰዎች ዘመን መረብ ጥለሃል። በቢሊ ሰንዴይ ዘመን፡ በዘመናት ሁሉ ላይ፡ መረብህን ጥለሃል።

134 አሁንም ባሕሩን እየመረመርክ ትገኛለህ። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ከእነዚህ መካከል አንዱ እዚህ ተቀምጦ ይሆንን? እዚህ ካሉ፡ በጉድጓዱ አጠገብ እንደነበረች ምስኪን ሴት ይሁኑ። በዝሙት አዳሪነቷም እንኳ፡ መሢሕ መሆንህን አወቀች። ያንን ምልክት አይታለችና። አበቃ። "አንተ ነቢይ እንደሆንክ ተረድቻለሁ፡" አለች። መሲሕ ሊሆን እንደሚችል ግን አላወቀችም ነበር። በሌላ አነጋገር፡ "መሲሑን እየጠበቅን ነው፡" አለችው። "መሢሑ በሚመጣበት ጊዜ፡ ሁሉንም እንደሚነግረን እናውቃለን።" አንተም "መሲሑ እኔ ነኝ፡" አልካት። አበቃ።

135 አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ "እኔ ነኝ፣ አትፍሩ። ይህ ቃል ኪዳኔ ነው፡" ያልከውን መመልከት ይሁንላቸው። ጌታ ሆይ፡ የታመሙትን ፈውሳቸው፡ የጠፉትን አድናቸው፡ ባዶውን ሙላ።

136 ዛሬ ማታ ሰንሄድ፡ በልባችን ውስጥ፡ ልክ እንደ እነዚያ፡ ከኤማሁስ እንደመጡ ሰዎች፦ "ዛሬ ማታ በሕንፃው ውስጥ፡ በመለኮታዊ መገኘት ሲያገለግለን ልባችን በውስጣችን አልተቃጠለምን" ማለት ይሁንልን! አንተ እንደሆንክ እንዴት አወቁ፡ ወደ ውስጥ ጋበዙህና ዓይኖቻቸው ተከፈተ። ዛሬ ማታ፡ እያንዳንዳችን፡ እንጋብዝሃለን። ባንረዳውም እንኳ፡ አንተን፡ መጋበዝ ይሁንልን። ራስህን ልትገልጥ የምትችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው።

137 ከትንሳኤህ በኋላ ራስህን የገለጥክበትን መንገድ እናስተውላለን፡ ከመስቀልህ በፊት እንዳደረግኸው በተመሳሳይ መንገድ አንድ ነገር አድርገሃል። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታም ና፡ "ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው እንደሆንክ ተናግረሃልና።" እዚህ ምድር ላይ፡ በሥጋ ቆመህ፡ እንዳደረግከው፡ደግመህ አድርግልን። ልክ እንደነዚያ፡ ልባችን በርቶ፡ ወደ ቤት እንሄዳለን። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

138 አሁን በአገልግሎት ላይ፡ ዛሬ ማታ፡ በጣም ሞቃት እንደሆነ አውቃለሁ፡ በጊዜ ለመውጣት ሀያ ደቂቃ አለን። [ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ አለ—አርታዒ።] እኔ…

139 የማደርገውን ነገር ማቆም ወይም መቆጣጠር አልችልም። አንድ ነገር ይመራኛል፡ ሁሌም በሕይወቴ በሙሉ፡ ይመራኛል፡ ሁሌም ትክክል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ነገር በቀር ምንም ነገር አልነገረኝም። እሱን ማቆም አልችልም። ምንም ማድረግ አልችልም። እንደምንም፡ እንዲሁ ይሰራዋል። ታዛዥ ከሆንኩ፡ እርግጠኛ ነኝ፡ ይህ የሚያስፈልገው አንድ ሰው አለ። እኔም ታማኝ እሆናለው። በዚያን ቀን፡ ታላቁ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፡ "የማንም ሰው ደም በእጄ ላይ የለብኝም፡" ማለት እፈልጋለው። አሃ-ሃህ። እ— እውነቱን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እንደኔ አይሁን… እወዳችኋለውና።

140 ህጻን ልጅ ቢኖርሽ ኖሮ... አንቺ ቀደም ሲል የገሰፅኩሽ፡ እመቤት፡ እናንተም ፀጉራችሁን ያሳጠራችሁና፡ ሌሎች ነገሮችን ያደርጋችሁ እህቶች እሰኪ አሰቡት። ለምሳሌ... ህጻን ልጃችሁ መንገድ ላይ ቁጭ ቢል፡ እናንተም እንዲህ ትሉታላችሁ፡ "የኔ ልጅ፡ ውዴ፡ ወደዚህ ብትገባ ይሻላል፡ ውዴ። ምናልባት፡ እንጃ፡ ምናልባት በአጠገብህ ልነዱ ይችላሉ።" ይህ ማለት ልጁን አትወዱትም። በትክክል። ወጥታችሁ ቆዳው እሰኪነሣ ድረስ ትገርፉታላችሁ፡ ወይም እንዲገባ ታደርጉታላችሁ። በትክክል። ትወዱታላችሁ።

141 ወንጌሉ እንዲህ ነው። እግዚአብሔር ይወዳችኋል። "እርሱም የሚወደውን ይገሥፃል፡ ወደ እርሱ የሚመጣውን ሕፃን ሁሉ ይቀጣቸዋል ይገሥፃልም።" ተግሣጽን መቋቋም ካልቻላችሁ፡ ትታችሁ ሄዳችሁ የምትናደዱ ከሆነ፡ ከዚያም የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም፡ ዲቃላ ልጆች ናችሁ ማለት ነው። ሰለዚህ አሰታውሱ፡ ቅዱሳት መጸሕፍት ናቸው።

142 አሁን ከእርሱ የሚወጣ አንድ ቃል፡ አንድ ቃል፡ በሚልየን በህይወቴ ዘመን፡ መናገር ከምችለው ሁሉ ይበልጣል። እርሱ ነው። የገባውን ቃል እናውቃለን። ምን ለማድረግ ቃል እንደገባም እናውቃለን። አሁን አላውቅም... እኛ... ከ...

143 ዳግመኛ ካርዶችን ሰጥቷል? ዛሬ ካርዶችን ሰጥተሃል´ዴ? ምን ነበር? ጄ፡ መልካም። መልካም፡ ጊዜ ለመቆጠብ፡ ከአንደኛው ቁጥር እንጀምር። አሁን፡ ምናልባት በሕንጻው ሁሉ ላይ ናቸው። ጄ፡ ቁጥር አንድ።

144 አሁንም አንዳንድ እንቅፋቶች አሉን። አንድ ጊዜ፡ **ከዚህኛው**፡ ጀመርን፡ ከጊዜ በኋላ፡ አንዳንዶች ወደ ኋላ እና ወደ ፊት፡ ዙርያውም፡ ነገር ግን እዚህ አከባቢ ሲታገሉ ነበር። ነገር ግን፡ በየቀኑ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ፡ ወደ መሰመሩ የመግባት እድል አላቸው። ያ ማለት እዚህ ሰለቀረባችሁ አይደለም...

145 በዚህ ሰብሰባ ውስጥ፡ እዚህ ከተፈወሱት ሁለት እጥፍ የሚጠጉ ሰዎች፡ በጉባኤው ውስጥ ሆነው እንደተፈወሱ፡ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? በትክክል፡ ታውቃላችሁ። አያችሁ፡ ሰለዚህ ይህን ማድረግ እንደለመዳችሁት፡ የጸሎት ካርድ በቀላሉ ሰዎችን ወደዚህ ለማምጣት፡በመካከላቸው መንፈሰ ቅዱሰን ለማግኘት ብቻ ነው የሚጠቅመው። አሁንም መያዝ እንኳ አያሰፈልገንም። የጸሎት ካርዶቹን መተው እንችላለን።

146 ትናንት ማታ እንዳደረግነው፡ ትናንት ማታ የጸሎት ካርዶ በጭራሽ አልነበሩንም። መንፈሰ ቅዱሰ የጸሎት ካርድ ባልያዙ ሰዎች መካከል መጣ። ብዙ ነገሮችን አይቻለሁ ሰለዚያ ምንም ነገር አልተናገርሁም፡ ምክንያቱም እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን አላውቅም። አሁንም በላያቸው የሚያንዣብብ ጨለማ አለ፡ ዝም ብዬ ትቼዋለሁ። አላውቅም። እነሱን መጥራት ምንም አይጠቅምም። የሚናገረው ሁሉ ትክክል ነውና፡ ሰለዚህ የሚናገረውን ሰሙ።

147 አሁን ጄ ነበር አልክ? ጄ፡ ቁጥር አንድ? ጄ፡ ቁጥር አንድ። የጸሎት ካርድ ያለው ማነው? እጅህን አንሳ። ልጄ፡ ተሳሰተህ መሆን አለበት፡ አንድ ሰው መኖር ነበረበት... ኦህ፡ ይቅርታ። ኦህ፡ እዚያ ከኋላ ካለው ግድግዳ በሰተጀርባ። ወደዚህ ነይ፡ እመቤት። ካ—ካርዶቹን ያመጡት አሁን ነው፡ ልጁ፡ ወንድም ቦርደርሰ፡ ወይም ቢሊ፡ አንዳቸው፡ አንዳንድ ጊዜ ሁለቱም፡ ከእናንተ በፊት እነዚህን ካርዶችን ያቀላቅሉና፡ ከዚያም የፈለጋችሁትን፡ ካርዳችሁን

ይሰጣችኋል። እናውቅም፡ እነሱ ዝም ብለው ይሰጣሉ... **ይሄኛው** አምስት ቁጥር፡ **ያኛው** ሰባት ቁጥር ሊያገኝ ይችላል፡ **ይሄኛው** አሥራ አምስት ቁጥር ሊያገኝ ይችላል፡ **ያኛው** ዘጠና-አምስት ቁጥር ሊያገኝ ይችላልና፡ እናውቅም። ከዚያም፡ እንደገና፡ ሰመጣ፡ የቱንም ይሁን በልቤ ያሰቀመጠውን፡ ዝም ብዬ ከዚያ እጠራለሁ፡ የትም ብሆን፡ ከዚያ እጠራለሁ። እ... አንዳንድ ጊዜ በ... በአንድ መሰመር ሰንት እንዳለ እቈጥራለሁ፡ በዚህ መሰመር ውሰጥ ባሉ ሰዎች እከፍላለሁ እና መልሱን አገኛለሁ። አያችሁ? ከዚያም፡ እንዲህ ያማላደርግ ከሆነ፡ ለምን፡ ዝም ብዬ... መጀመሪያ ወደ አእምሮዬ የሚመጣውን፡ እጠራለሁ።

148 ቁጥር አንድ። ጄ፡ ቁጥር ሁለት። ቁጥር ሁለት፡ ቁጥር ሦሰት፡ ቁጥር አራት፡ ቁጥር አምሰት፡ ቁጥር ሰድሰት፡ ሰባት፡ ሰምንት፡ ዘጠኝ፡ አሥር፡ ይምጡ፡ አያችሁ። አንድ፡ ሁለት፡ ሦሰት፡ አራት፡ አምሰት፡ ሰድሰት፡ ሰባት፡ ሰምንት፡ ዘጠኝ፡ አሰር። ጥሩ ነው። መንገዱ ያ ነው፡ ቀጥ ብለህ ና... ቆይ እንደኛው በ... በሌላ መንገድ ሄደ። አንድ፡ ሁለት፡ ሶሰት፡ አራት፡ አምሰት፡ ሰድሰት፡ ሰባት፡ ሰምንት፡ ዘጠኝ። ትክክል ነው። አሁን፡ እዚህ፡ እነሆ፡ አሥር ቁጥር። መልካም።

149 አሥራ አንድ፡ አሥራ ሁለት፡ አሥራ ሦሰት፡ አሥራ አራት፡ አሥራ አምሰት። አምሰት ተጨማሪ ነው። አንድ፡ ሁለት፡ ሦሰት፡ አራት፡ አምሰት። መልካም፡ ጥሩ ነው።

150 አሰራ ሰድሰት፡ አሰራ ሰባት፡ አሰራ ሰምንት፡ አሰራ ዘጠኝ፡ ሃያ። አንድ፡ ሁለት፡ ሶሰት፡ አራት። አራት ብቻ ነው የማየው። ሃያ፡ ሃያ አቤት አለ? መልካም። አሁን፡ በአንዴ ብዙ እንዲቆም አንፈልግም። አሁን ከእነዚህ ጋር የምንቆይ ከሆነ፡ በቂ ነው፡ ተጨማሪ እንጠራለን። ላንጠራ እንችላለን... ምናልባት...

151 ጥቂት ተጨማሪ እንሞክር። አምሰት ተጨማሪ እንሞክር። ሀያ-አንድ እሰከ ሀያ-አምሰት፡ በጄ ውሰጥ፡ የምትፈልጉ ከሆነ እንዲቆሙ አድርጓቸው። ከሀያ-አንድ እሰከ ሀያ-አምሰት። አንድ፡ ሁለት፡ ሦሰት፡ ወደ ኋላ፡ አራት። አንድ፡ ሁለት፡ ሦሰት፡ አራት፡ ያ አምሰት ነው። እሺ፡ አሁን እዚህ ላይ እናቁም። በመሰመሩ ውሰጥ ሀያ-አምሰት አሉ፡ እዚህ ላይ እ—እየተሰለፉ ነው።

152 አሁን አንድ ውለታ ልጠይቃችሁ። ለ... ለሚቀጥሉት አሥራ አምሰት፡ አሥራ ሰድሰት ደቂቃዎች፡ ሙሉ ትኩረታችሁን ለእግዚአብሔር ሰጡ። ያንን ታደርጋላችሁ? ይህን ታደርጋላችሁ፡ ልባችሁን ትከፍታላችሁ? አሁን የተናገርኩትን አሰታውሱ። በዳክዬ ጀርባ ላይ እንደሚፈሰ ውኃ፡ ተብሎ በተረት እንደሚተረተው፡ በጀርባችሁ ላይ እንድፈሰ አትፍቀዱ። ይህን አታድርጉ። ይህን አሰቡ።

153 በቅዱሳት መጻሕፍት ውሰጥና፡ በዘመኑ ተሰፋ ውሰጥ የሌለ ነገር ከተናገርኩ፡ እዚህ ሥራ እሰኪያጄን ለመናገር መጥታችሁ ለእኔ የመናገር መብት አላችሁ። ትክክል ነው። የ—የማሰተምረው በቃሉ ውሰጥ ያለውን ብቻ ነው። በዚያም ቃል በትክክል ከጸናሁ፡ በዚያ መንገድ ከተናገርኩ፡ እግዚአብሔር... በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ አለ። የጌታ መልአክ በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ ያልሆነ ነገር ቢነግረኝ፡ የጌታ መልአክ አይደለም። ትክክል ነው። በቅዱሳን መጻሕፍት ውሰጥ ከሚገኘው ቃል በሰተቀር አንድም ነገር ነግሮኝ አያውቅም፡ ለዚህም ምሰክር ትሆናላችሁ። ከመቶ ሺዎችና፡ ከሺዎች

እና ከዓለም ቋንቋዎች ውስጥ፡ አንድም ነገር ተናግሮ አያውቅም፡ አንድም ጊዜ የተሳሳተ ነገር አይናገርም፡ ወይም የማይሆን ነገር አይናገርም።

154 አዳምጡ። ሥራ እስኪያጁን እና ሌሎቻቸውን ጠይቁ። እዚህ የምታዩት ሁሉ፡ የእሱ የአማተር ጎኑ ነው። ወንድሞች ሆይ፡ ትክክል ነውን? [ወንድሞች፡ "በትክክል" አሉ።—አርታዒ።] ለምን፡ እዚያ፡ በግል ሕይወት ውስጥ፡ እንደሚለው ነው፡ "**ወደዚህ** ቦታ ውረድ፡ **ይህን** ቦታ ተመልከት። **ይህ** ይሆናል። **ይህን** እዚህ፡ **እንዲህ** በል።" በየጊዜው፡ በየዓመቱ፡ አያችሁ፡ ያለማቋረጥ ነው። በጉባኤ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚመለከቱት ትናንሽ—ነገሮችን ብቻ ነው። አሁን ግን ትሁታን ከሆናችሁ።

155 በዚህ የጸሎት መሰመር፡ ውስጥ የቆማችሁ ሁሉ፡ ለእኔ እንግዳዎች ናችሁ? ከሆናችሁ እጃችሁን አንሡ። መልካም። ስለ እናንተ ምንም የማውቀው ነገር እንደሌለ፡ የምታውቁ ሰንቶች ናችሁ? እጃችሁን አንሡ። አሁን… አመሰግናለሁ። የት እንዳላችሁ ግድ የለኝም፡ በረንዳ ላይ ብትሆኑ፡ ወደ ኋላ ከግድግዳው በስተጀርባ፡ **እዚህ** በኩል፡ የትም ብትሆኑ ግድ የለኝም። እኔ…

156 አሁን፡ ይህ ለጥቅማችሁ ነው። ይህ ለጥቅማችሁ ነው። አያችሁ፡ ይህ ለጥቅማችሁ ነው።

157 የሚናገረኝ የልጅ ልጄ መሰሎኝ ነበር፡ ግን አልይደለም። ዛሬ ማታ፡ እዚህ የሆነ ቦታ ህጻኑ የልጅ ልጄ አለና፡ ይህን የሚያክል ነው፡ ታናሹ ፖል መሰሎኝ ነበር። ሁሌም መጥቶ፡ በመድረኩ ላይ ቆሞ፡ እንደሚሰብክልኝ ይናገራል፡ ገና ሁለት ዓመት እንኳ አልሞላውም። ይህ ህጻን ልጅ እናቱን እየፈለገ ይመሰለኛል።

158 ስለዚህ አስታውሱ፡ እናንተን ለመርዳት እየሞከርኩ ነው። እ… እግዚአብሔር ይህን ያውቃል። ልረዳችሁ እየሞከርኩ ነው፡ አያችሁ። አሁን ተመልከቱ፡ እሱ ወደመካከላችን ከመጣ፡ እንድትጠቀሙ እፈልጋለሁ።

159 አሁን አስቡት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ዘመን አደርጋለሁ ብሎ ቃል በገባው መሠረት፡ በሥጋ እየተራመደ እየሰራ ነው። ይህን ቃል እንደገባ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ያን ጊዜ መልአኩ ጀርባውን አዙሮ፡ ልክ በሰዶም ላይ እንዳደረገ ነው፡ ስለዚህም… .ያም እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር እንደነበር ታምናላችሁ? እሰኪ እግዚአብሔር ነው የምትሉ? ["አሜን።"] በትክክል፡ እሱ ነው። መጽሐፍ ቅዱሰም እንደነበረ ይናገራል። እርሱ፡ ኢየሱስም፡ ጠቅሶ ተናግሯል። አሁን አስተውሉ።

160 አሁን የጸሎት ካርድ ያልደረሳችሁ ሁሉ፡ የትም ብትሆኑ፡ አንድ ነገር እንድታደርጉልኝ እፈልጋለው። አሁን እነዚህን ነገሮች፡ አስታውሱ፡ እንደተፈወሳችሁ ሲነገራችሁ፡ ወይም ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ሲነገራችሁ አስተውሉ። የሚናገረውን ልብ በሉ። ከተናገረ፡ እምነታችሁን ለማጠናከር ነው። እምነታችሁ ወደ አንድ ቦታ ሲደርስ፡ በቀላሉ ደርሳችሁ ጌታን ትቀበላላችሁ። እኔ አይደለሁም፡ ምክንያቱም የሰማይ አባት ያውቃል።

161 እዚህ መሰመር ላይ ሰመለከት፡ የማውቀውን አንድ ሰው አላየሁም። በጠቅላላው ጉባኤ ውስጥ እኔ የማውቃቸውን ሁለት ወይም ሦስት ሰዎችን ብቻ፡ ማየት እችላለሁ። አሁን፡ ስለማላውቅ፡ አንድ አሳየኝ፡ ማለት እችላለሁ። ኤድመንድ ዌይ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እዚህ እንደነበር አውቃለሁ። እሱን ያ—ያየሁት፡ መሰሎኝ ነበር…

162 ካልተሳሳትኩ፡ አንድ የማውቀው ሰው ይታየኛል፡ እሱና ሚስቱ፡ ፍሪዚንገር የተባለች ትንሽ ልጅ፡ ከኦሃዮ። አንተ ወንድም-... **ያኛው** ወንድም ፍሪትዚንገር ነህን? በተመሳሳይ መስመር ውስጥ ነበራችሁ... እነዚያ ወንድምና እኅት ፍሪዚንገር፡ ከኦሃዮ፡ ጓደኞቼ ናቸው።

163 ከዚያ ውጪ ደግሞ፡ እዚያ ከኋላ የተቀመጠው፡ ያኛው... በዚህ በኩል፡ የዘጠና-ሁለት አመት ሽማግሌ፡ ዊልያም ዳውች አያለው። እሱና ባለቤቱ ይታዩኛል። ነርስ ነች። ዊልያም ዳውች፡ በኦሃዮ፡ የቅርብ ጓደኛዬ ነው። በቅርብ ጊዜ፡ በዘጠና-አንድ ዓመቱ፡ የልብ ህመም፡ የልብ ድካም፡ አጋጥሞት ነበር፡ ሚስቱም በፍጥነት ና፡ ብላ ጠራችኝ፡ እየሞተ ነበር። ያን ጊዜ...

164 ለእኔ ለየት ያለ የቅርብ ወዳጄ ነው። እሱን ለማየት ስሄድ፡ ተጨንቄ ነበር። እናም ቆምኩ፡ አንዱ ጎማዬ ከመስመር ወጣ፡ ጎማዬን ብጥስጥስ አርጎብኝ ነበር፡ ወደ ቴክሳኮ ጣቢያ ሄድኩ፡ ጋዝ ቀዳሁ፡ እነሱም መጥተው፡ ፈተሹት። ወደ ላይ ተመለከትኩና፡ ወንድም ዳውች በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ እየሄደ፡ እጄን ሲጨብጥ አየሁ። “ጌታ ይባረክ፡” አልኩ። ወደ ኋላ ተመለከትኩ፡ እነሆ ጎዳናውን አልፎ መጣና፡ እጄን ጨበጠኝ። ከዚያም ወደ እርሱ ሄድኩ።

165 አንድ ወጣት አይሁዳዊ፡ ወይም መካከለኛ-ዕድሜ ያለው፡ አይሁዳዊ፡ ዶክተሩን አገኘሁት። እኔም “ዶክተር፡ እንዴት ነው፡” አልኩት?

166 እርሱም “የመታገል እድል እንኳን አላገኘም፡” አለኝ። “ኦክሰጅን ተገጥሞለታል፡” አለኝ። “እዚሁ ይሞታል፡” አለኝ። “ዘጠና-አንድ ዓመቱ መሆኑን፡ አትርሣ፡” አለኝ።

“እሺ፡ ወዳጄ፡” አልኩት።

167 “ልቡ ሙሉ በሙሉ ተዳክማለች፡ ምንም ማድረግ አይቻልም።” አለኝ። “አሁን ይሞታል፡” አለኝ።

168 እኔም “እሺ፡ ወዳጄ። ግን፡ በጭራሽ፡ አይሞትም። ይኸው ነው” አልኩት።

169 ወደ ውስጥ ገባሁ፡ እጄን በኦክሰጅን ቱቦ ሥር አኖርኩት። እንዲህ አልኩት፡ “ወንድም ዳውች፡ትሰማኛለህ? ” ቀና ብሎ አየኝ። አሁን በእውነቱ፡ በሰሙ፡ ጀርመናዊ ነው፡ D-a-u-g-h፡ ዳውች ብዬ እጠራዋለሁ፡ አያችሁ። እጄን በኦክሰግን ቱቦ ሥር አ—አድርጌ፡ እንዲህ አልኩት፡ “ትሰማኛለህ፡ ወንድም ዳውች” አልኩት?

እርሱም “አዎን፡” አለኝ።

“አንተ አትሞትም፡ እንደማትሞት አይቻያለሁ።” አልኩት።

170 ከሳምንት በኋላ፡ በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ቆሜ ሳለሁ፡ ወንድም ዳውች ራሱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እየተራመደ መጣ! ከሰብሰባው በኋላ ወንዙን አቋርጬ፡ ለመብላት፡ ወደ አንድ ካፊቴሪያ ሄድኩ። ከመኪናዬ ወጥቼ፡ ጎዳናው ላይ እየሄድኩ ሳለ፡ ወንድም ዳውች እጁን ዘርግቶ መጣ። ያየሁት ራዕይ አልወደቀም።

171 ይህ የዘጠና-አንድ ዓመት አዛውንት፡ በካሊፎርኒያ የተደረገውን፡ እያንዳንዱን ጉባኤ ተከታትሏል። ወንድም ዳውች፡ ህዝቡ እውነተኛ ወታደር ምን እንደሆነ ያይ ዘንድ። በተቀመጥቅበት፡ እጅህን ማንሣት ትችላለህ? እዚህ፡ ቁጭ ብሎ፡ አያችሁ፡ የዘጠና-አንድ ዓመት ሽማግሌ፡ እያንዳንዱን

ሰብሰባ ይከታተላል። እዚህ ተብርናክል ከሆንኩኝ፡ ትንሽ ሰብከት ሰሰብክ ለመሰማትና፡ ተመልሶ ለመሄድ፡ በየቀኑ በመቶዎች የሚቈጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ይነዳል። እግዚአብሔር ሆይ፡ "እነሆ ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።"

172 እንዲህ አልኩት፡ በቀደም ከእሱ ጋር ሰነጋገር፡ "ወንድም ዳውኙ፡ ምን ላደርግልህ፡" አልኩት?

173 "ወንድም ብራንሀም፡ አንድ ጥያቄ ብቻ አለኝ። እርሱ ሲመጣ፡ አብሬው መሄድ እፈልጋለሁ።"

174 "አትጨነቅ። ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። እርግጥ ነው፡" አልኩት። አሁን፡ ሰውዬው መጣ፡ ተጠመቀ፡ ኦህ፡ የመንፈሰ ቅዱሰን ጥምቀትና ሁሉንም ነገር ተቀበለ፡ የክርሰቶሰ ድንቅ አገልጋይ ብቻ ሆነ።

175 አሁን ሰው ሁሉ፡ ትሁት እንዲሆን፡ ይህን መንገድ ተመልክታችሁ እንድትጸልዩ፡ እጠይቃለሁ።

176 አሁን፡ እዚህ ካላችሁ አሰተማሪዎች እርሱ ሊቀ ካህን መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ፡ በድካማችን ሰሜት ሊነካ እንደሚችል የምታውቁ? መልካም፡ እሱ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም፡ ያው ከሆነ፡ ያው ሊቀ ካህን ከሆነ፡ በተመሳሳይ መንገድ ይሠራል። ብቻ፡ እርሱ፡ አካሉ በ... በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ነው። ሰንቶች ታውቃላችሁ? ["አሜን።"] የኢየሱሰ ሥጋ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ነው። ነገር ግን "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ብሎ ቃል በገባው መሰረት ራሱን ለመግለጥ ሰውነታችንን ይጠቀማል።

ዝም ብላችሁ እንድትቀመጡ፡ በትሕትና፡ እንድትጠባበቁ፡ እንድትጸልዩ እጠይቃችኋለው።

177 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ የገባኝን ያህል ትሁት ለመሆን ሞክሬአለሁ። አሁን ጌታ ሆይ፡ ከአንተ ዘንድ አንድ ቃል ብቻ ይምጣ፡ ከዚያም ጸጥ ያለ፡ ትንሽ ድምጽ ወደ ጉባኤው ይምጣና እንዲህ ይበል፡ "እኔ ነኝ፥ አትፍሩ።" ይሁንልን፡ አባት ሆይ። ዛሬ ማታ በተሰበከው መልእክት፡ ቃልህ እንዲረጋገጥ፡ እራሴን ለአንተ አደራ እሰጣለሁ። ይህን ማድረግ አይጠበቅብህም። ማድረግህ ግን፡ ወይም ብታደርገው ግን፡ ምክንያቱ ቃል ሰለገባህ ነው። በኢየሱሰ ሰም፡ ይህን እንድታደርግ እጸልያለሁ። አሜን።

178 ሰው ሁሉ በትህትና ይሁን፡ እውነተኛ ትህትና። እንዴት ነሽ? አሁን ሰንቀጥል ጥቅሰ እሰጣችኋለሁ። ጌታ ካደረገ፡ አላውቅም። ነገር ግን-... ቅድም በዚያ መልኩ እየሰበክኩ ነበር፡ አያችሁ፡ ያ ሌላ ዓይነት ቅባት ነው። ይህ ደግሞ ሌላ ዓይነት ቅባት ነው። ያ በረከት ብቻ ነበር። ይህ፡ አንድ ነገር ነው፡ በቀጥታ ሕይወታችሁን ከእናንተ ይወሰዳል።

179 አሁን እዚህ የቆመችው ሴት። በሕይወቴ ውሰጥ አይቻት አላውቅም። እንተዋወቅም? ከጥቅት ደቂቃ በፊት፡ አላውቅህም፡ እንዳልሽ እምናለው። እግዚአብሔር ያውቅሽል። እኔንንም ያውቃል። አሁን እዚህ ለምን እንደቆምን ታውቂአለሽ፡ በፍርድ ቀን መልሰ እንደምንሰጥበት ታውቂአለሽ? [ያቺ እህት፡ "አሜን" አለች።—አርታዒ።] ይህን ታውቂአለሽ? አሁን የምናደርገውን ነገር፡ እግዚአብሔር በዚያ ሰማይ መልሰ እንድንሰጥበት እንደሚያደርገን ታውቂአለሽ? ይህን ያልኩት በዓላማ ነው። አሁን፡ ጌታ ኢየሱሰ በአዕምሮሽ

ውስጥ ያለውን፡ ምን እየሠራሽ እንደሆነ፡ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር፡ ቢገልጥልኝ ታምኚያለሽ? ይህን ማመን አለብሽ፡ አይደለም'ዴ? [አሜን።"]

180 እናንተስ ጉባኤ ሁላችሁ፡ ታምኑታላችሁን?

181 አሁን ልክ በጉድጓዱ አጠገብ እንደነበረችው ሴት ቆመናል፡ ጌታችንም፡ ወንድና ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኙ። አያችሁ? እነሆ እኛም፡ እየተገናኘን ነው... ይህም ቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ነው። አሁን መንፈስ ቅዱስ ሲናገር... የመጣሽው ለሌላ ሰው ይሁን፡ ታመሽ ይሁን፡ በቤት ውስጥ ችግር ይኑር፡ የገንዘብ ችግር ይሁን፡ ምንም ይሁን ምን፡ ምንም ዕውቀት የለኝም። እሱ ግን ያውቃል። በልብሽ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ግን መለየት ይችላል። እርሱ ቃል ነው። እኔ አልችልም። እኔ ሰው ነኝ። ይህን የማደርግበት ምክንያት ይህ ነው፡ አየሽ፡ ስለተጨነቅሽ ነው።

182 ከችግሮችሽ አንዱ፡ የጭንቀት ስሜት አለብሽ። ትክክል ነው። እንዲሁም የስኳር ሕመም አለብሽ፡ ይህ ደግሞ ሌላ ያለብሽ ችግር ነው። ትክክል ነው። ተግዳሮቶች፡ ብዙ ችግሮች አሉብሽ። ልክ ነው? ትክክል ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። አየሽ? እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? [ያች እህት፡ "አምናለው" አለች።—አርታዒ።] ታምኚያለሽ? አሁን፡ የጭንቀት ስሜትሽ ከእድሜሽ የተነሳ ነው፡ አየሽ፡ አሁን ግን ያ ሁሉ ይተውሻል። በእምነት ወደ ቀራንዮ እንሄዳለን፡ የደም ለውጥ እናደርጋለን የሚል እምነት አለኝ።

183 አሁን፡ ኢየሱስም ያደረገው ይህንኑ ነው። ለሴቲቱ ምን ችግር እንዳለባት ነገራት። ብዙ ባሎች ነበሯት። የአንቺ ደግሞ... የአንቺ የጭንቀት ስሜትና፡ ሁለት ወይም ሦስት ተጨማሪ ነገሮች እና ችግሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ። ትክክል ነው፡ አይደል? ተመሳሳይ ነገር ነው።

184 አሁን፡ ወደ ሰምዖን በመጣ ጊዜ፡ ማን እንደ ሆነ ነገረው። እግዚአብሔር ስምሽን ማን እንደሆንሽ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? የበለጠ እንድታምኚ ያደርግሻል? ያደርግሻል? ወይዘሮ ስትሮንግ... [ሴቲቱም፡ "ስታውት።" አለች—አርታዒ።] ስቶት፡ ታምኛለሽ? ሂጂና እመኚ፡ እነሆ... እልቋል። አሜን።

185 ነይ። ታምኛለሽ? እኔና አንቺ አንተዋወቅም። አላውቅሽም። እግዚአብሔር ያውቅሻል። ችግርሽ ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? ከነገረኝ፡ ከዚያ ጌታ እግዚአብሔር ይመስገን። እውነት ነው? [እህት፡ "አዎን፡ እውነት ነው" አለች።—አርታዒ።] አሁን መጨነቅ አ—አያስፈልግሽም፡ አየሽ፡ ያ የሚሰማሽ፡ ያ—እሱ ነው። መልካም። እንዲሁም የነርቭ ችግር፡ በአእምሮ ነርቭ፡ በቀላሉ ትሸነፊያለሽ። የደም ቧንቧ ችግር፡ የጉበት ችግር፡ እንዲሁም የደም ማነስ አለብሽ። ትክክል ነው። የሆነ ነገር አለብሽ...

186 ሰው ሆኖ እዚህ መታየቱን ይቀጥላል። እግዚአብሔር ሊፈውስሽ እንደሚችል ታምኛለሽ? [ሴቲቱም፡ "አዎን፡ አምናለው" አለች።—አርታዒ።] ባለቤትሽንም፡ እሱንም፡ ይፈውሰዋልን? የሆድ ህመሙ ሊወገድለትና፡ ጤነኛ ሊሆን ይችላል ብለሽ ታምኛለሽ? እየተሰቃየ ያለው በዚህ ነው። ሄደሽ እጆችሽን በእርሱ ላይ አኑሪ፡ እንዲህ ንገሪው፡ ይ—ይተወዋል።

187 ለአንቺ እንግዳ ነኝ። ጌታ ኢየሱስ ሁለታችንም ያውቃል፡ አይደል? እግዚአብሔር እንዲፈውስሽ ታምኛለሽ? ጌታ ኢየሱስ በ... በልብሽ ውስጥ ያ... ያለውን ነገር ቢገልጥልኝ፡ ይፈውስሻል ብለሽ ታምኛለሽ? አንዳንድ

ችግሮች አሉብሽ። አንድ ነገር፡ የ—የ—የሽንት ቧንቧ ችግር አለብሽ። ሌላ ነገር ደግሞ፡ የሽንት ቧንቧሽ እንዲቆሰል ምክንያት ሆኗል፡ ነገር ግን ዶክተርሽ የተናገረው ያንን ነው። አሁን፡ ሌላኛው ነገር፡ ደግሞ ለዚያ ሲባል ቀዶ ጥገና ማድረግ ይፈልጋሉ። ያ በትክክል ትክክል ነው። እውነት አይደለም? አሁንስ ይህን ማለፍ እንደሚችል ታምኛለሽ? በእሱ ላይ እምነት እንዳለሽ ታስብያለሽ? አሁን ይህን የማደርገው እኔ እንዳልሆንኩ ታውቅያለሽ። ታምኛለሽ? መልካም። ሂጂ፡ እንደ እምነትሽ፡ ይሁንልሽ።

188 ሁለታችንም አንተዋወቅም፡ ብዬ እገምታለሁ። ጌታ እግዚአብሔር ሁለታችንም ያውቃል። እንችን የሚረዱ ነገሮች ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? [ሴቲቱም "አዎን፡ አውቀዋለሁ፡" አለች።—አርታዒ።] እንዲሁ እንደሚያደርግ ታም ታምኛለሽ። ["አዎንታዊ።"] እያልኩ ያለሁት... "አዎንታዊ፡" በጣም ጥሩ። ያ በጣም ጥሩ ነው። አሁን ብዙ ችግር አለብሽ፡ ብዙ ውስብስቦችና ነገሮች አሉብሽ፡ እንደ ሳል ያለ ነገር፡ መቋቋም አቅቶሻል። በጣም ተጨንቀሻል። ያም—ያም፡ ትክክል ነው።

189 ከዚያም፡ በልብሽ ላይ ሸክም አለብሽ፡ ያም ሸክም ለአንድ ሰው ማለትም፡ ለልጅሽ ነው። እሱ ችግር አ—አጋጥሞታል፡ አንዳንድ የቤት ውስጥ ችግሮች። እሱና ሚስቱ ሁሌም ይጨቃጨቃሉ... ? ... አንቺም በዚህ ሸክም ተሰምቶሻል። ትክክል ነው። አሁን በሙሉ ልብሽ እመኚ፡ ሁሉም ነገር ይወገዳል ይጠፋል። አሁን እመኚ። ጌታ ይባርክሽ።

190 እንዴት ነህ፡ ወዳጄ? ለአንተ እንግዳ ነኝ፡ አ—አንተም ለእኔ እንግዳ ነህ። እና—እና አሁን ይጀምራል... አሁን ያየኋቸው፡ ራዕዮች፡ ቤቱ በሙሉ በብርሃን የተሞላ ይመስላል፡ ልክ የሚሽከረከር-ብርሃን አይነት። አየህ? ጌታ ኢየሱስ ግን የቆምክለትን ነገር ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምናለህ? እንደሚያደርግ ታምናለህ? እኔ ራሴ፡ እምናለሁ። ከመንፈስህ ጋር፡ ለመገናኘት ብቻ ነው፡ የምናገረው። አየህ፡ አላውቅህም፡ ስለዚህ ይህን የሚያደርግ ከእኔ ሌላ የሆነ ነገር አለ ማለት ነው። እኔ ራሴን ሙሉ በሙሉ ከራሴ ማራቅ አለብኝ፡ እሱ ራሱ ያደርገዋል። ተረዳህ?

191 አሁን፡ አንድ ነገር፡ አንተ በከባድ የነርቭ ሕመም እየተሰቃየህ ነው፡ እናም ይህ የነርቭ ሕመም ለተወሰነ ጊዜ ቆይቷል። ትክክል ነው። ያ የነርቭ ሁኔታ፡ ከፍተኛ የደም ግፊት እንዲኖርህ ምክንያት ሆኗል። ደግሞም ስትሮክ አሞሃል። ያ ነው። አንተ ሰባኪ ነበርክ፡ ወይም፡ አሁን ሰባኪ ነህ። አሁን ሰባኪ ነህ፥ በመድረክ ላይ ስትቆም አይቻለሁ። ከዚያም፡ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ይኑርህ፡ ጭንቀቱም ይተውሃል። ሁሉም አገልጋዮች እንዲህ ዓይነት ችግር አላቸው። ደኅና ትሆናለህ። ወደ መድረክ ተመለስ፡ እግዚአብሔርን ታዘዝ እንዲሁም ለቃሉ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ሁን።

192 በወንበር ላይ የተቀመጥሽ፡ የጀርባ ሕመም እንደለቀቀሽ ታምኛለሽ? ታምኛለሽ? [ሴቲቱም፡ "አዎን" አለች።—አርታዒ።] ደህና፡ ወዳጄ፡ እንግዲያውስ ቀጥል፡ እንዲህ እያልክ፡ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ።"

193 ነይ፡ እመቤት። እንዴት ነሽ? የእርሱ አገልጋይ እንደሆንኩ ታምኛለሽ? [ሲቲቱም፡ "በርግጥ አምናለው" አለች።—አርታዒ።] መልካም። የሴት

ችግር፡ የሴቶች ችግር፡ ለቆሽ እንደሚሄድ ታምኛለሽ? [“አሜን።”] አምነሻል? እንግዲያውስ እንዲህ እያልሽ፡ ቀጥይ፡ “አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ።”

194 የኩላሊት ችግር፡ በጀርባሽ ላይ፡ የጀርባ ችግር እግዚአብሔር ከበሽታሽ እንደሚፈውስሽና ደኅና እንደምትሆኚ፡ ታምኛለሽ? እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? መልካም፡ መንገድሽን ቀጥይ።

195 ነይ፡ እመቤት። ለአንቺ እንግዳ ነኝ። እኔ ፈጽሜ፡ አንዳች ባልናገርሽም እንኳ፡ የታመሙትን ለመፈወስ የእግዚአብሔር መገኘት እዚህ እንዳለ ታምኛለሽ? [ሴቲቱም፡ “በእርግጠኝነት፡ አምናለሁ” አለች።—አርታዒ።] አምነሻል? መልካም፡ ካመንሽ፡ የሆድሽ ህመም... ይኸው ተናግሬሽ ጨርሼለሁ፡ አየሽ። ጠ—ጠፍቷል። ነገርኩሽ፡ አየሽ።

196 እንዴት ነህ፡ ወዳጄ? እግዚአብሔር በልብ ውስጥ ይኖራል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ ልብህ ክፉኛ አሞሃል። እሱ ያስተካክለዋል ብለው ታምናለህ? እያመንክ መንገድህን ቀጥል። እግዚአብሔር ይባርክህ። ታምናለህ፥ ትክክል ያደርገዋል።

197 ተጨንቀሃል፡ የሆድ ሕመም እንዲኖርህ አድርጓል፡ የሆድ ቍስል እንዲኖርብህ አድርጓል። ከበላህ በኋላ ያስጨንቅሃል። አሁን ሁሉም እንደጠፉ ማመን ትችላለህ? ሂድ ለራስህ የሚበላ ነገር ብላ።

198 መነሳት በጣም ይከብድሃል፡ ጀርባህ በጣም አስጨንቆሃል። [ታካሚውም፡ “አዎን፡ ጌታዬ” አለ።—አርታዒ።] ካመንክ፡ ከእንግዲህ እያስጨንቅህም። ታምናለህ? [“አዎን፡ ጌታዬ።”] መልካም፡ ሂድ፡ ጌታ ኢየሱስም ሙሉ በሙሉ ይፈውስህ።

199 ይሄን ያህል የሚያስጨንቅህ ምንድነው? እንግዲያውስ፡ ሂድና “ከሁን በኋላ አልጨነቅም፡” በል፡ አትጨነቅምም። ሂድ እመንም። መልካም፡ ወዳጄ።

200 ነይ፡ እመቤት። አሁን፡ ኢትዮጵያዊት ሴት፡ እና ነጭ ሰው፡ ልክ በዚያ ቀን፡ ኢየሱስን እንደመገናኘት አይነት ነው። በደቡብ ውስጥ እንደነበረ ዓይነት መለያየት ነበረ፡ ከዚህ በኋላ ግን የለም። ኢየሱስ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ህዝቦች መሆናቸውን እንዲያውቁ አደረጋቸው። አይሁድ ወይም ሳምራዊት ትሁን፡ ምንም ልዩነት የለውም፡ አያችሁ።

201 አሁን፡ እግዚአብሔር ካልረዳሽ፡ አርትራይተስ በፍጥነት ሽባ ያደርግሻል። ግን እርሱ እንደሚረዳሽ፡ እንደሚፈውስህ ታምኛለሽ? ያችህ ሴት እንዳደረገችው ሁሉ፡ አንቺም ወደ ቤትሽ ሂጂና እግዚአብሔር ያደረገልሽን ታላላቅ ነገሮች ለወገኖችሽ ተናገሪ። መልካም።

አሁን፡ አንድ የቀዶ ጥገና ቢላዋውን ለማውጣት የተዘጋጀ ሀኪም አለ።

202 አንድ ደቂቃ። ይህች ሴት አይደለችም። አሁን፡ አንድ አፍታ ብቻ፡ ሁሉም ሰው አሁን ጸጥ ይበል። ሰ—ሰይጣን ነው፡ አንድ ነገር ለማድረግ ይፈልጋል። እነሆ። ሁለታችሁ ላይ እጢ፡ እጢ አለ። በትክክል። አንቺም እጢ አለብሽ፡ እሷም እጢ አለባት፡ ዲያብሎስም እርድታ ለማግኘት አንዱ ለአንዱ እየተጠራራ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስም፡ እየጮኸ ነው። ማንን ታምናላችሁ፡ እርሱን ነውን? መልካም። ከአልጋው ላይ ተነሺ፡ እመቤት። ከአልጋው ላይ ተነሺ። ከዚህ ተነሺ፡ እመኚም። ሂጂ፡ አሁን እርሱን እመኚ። አሜን።

203 ታምኛለሽ? ሁሉም ነገር ይቻላል። ታምኛለሽ? በጉባኤ ውስጥ ያላችሁስ?

204 አሁን በእግሮቻችን ዕንቁም። ይህን ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው። እያንዳንዱ ሰው... እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሁን ሰው ሁሉ በእግሩ ይቁም። እግዚአብሔርን አመሰግኑ። እጆቻችሁን አንሡ።

205 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ! ስለ ታላቅነትህና፡ የታመሙትን ስለፈወስህ እናመሰግንሃለን።

64-0307 የባሕሩ ላይ ምስክርነት
ሶልስ ሃርቦር ቴምፕል
ዳላስ, ቴክሳስ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org